# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 135 ጥር 15 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# የኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሁለተኛ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነፃ የጉብኝት ፕሮግራም አዘጋጀ

## - በትኬትና ሆቴል ላይ ከ15 እስከ 20 በመቶ የዋጋ ቅናሽ ተደርጓል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ለሁለተኛው ትውልደ ኢትዮጵያውያን ነፃ የጉብኝት ፕሮግራም ማዘጋጀቱን የኢትዮጵያ አየር መንገድ አስታወቀ። በአየር ትራንስፖርት ትኬትና በሆቴል አገልግሎቶች ላይ ከ15 እስከ 20 በመቶ የዋጋ ቅናሽ ማድረጉ ተገልጿል።

በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ የንግድ ዘርፍ ዋና ኃላፊ አቶ ለማ ያደቻ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን (ዶ/ር) ጥሪ ተቀብለው ለመጡ የሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን የነፃ ጉብኝት ፕሮግራም ተዘጋጅቷል።

አዲስ አበባ በሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ የጉብኝት ፕሮግራም መዘጋጀቱን ጠቁመው፤ ከአንድ መቶ በላይ እንግዶች ሙሉ ወጪያቸው ተሸፍኖ ለአንድ ቀን የከተማ ጉብኝት እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

የአየር መንገዱ "ኢቲ ሆሊዴይስ" ሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ጉብኝት መርሀ ግብርን ለመቀላቀል በተዘጋጀው ድረ-ገጽ አማካኝነት በመመዝገብ መሳተፍ እንደሚቻል አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ አየር... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# የባህር በር ስምምነቱ በዓለም መድረክ የመደራደርና የኃይል ሚዛንን የማስጠበቅ አቅምን ያሳድጋል

ገጽ 8



አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን

# መንግሥት ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ሰላም ለማስፈን በቁርጠኝነት እየሠራ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ሰላም ለማስፈን በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ገለጹ።

መንግሥት ግጭት... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ኢትዮ ቴሌኮም ከ74 ሚሊዮን በላይ ደንበኞችን አፍርቷል

## -የቴሌ ብር ተጠቃሚዎች ቁጥርም 41 ሚሊዮን ደርሷል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ቴሌኮም የደንበኞቹ ቁጥር ከ74ሚሊዮን በላይ መሆናቸውን እና የቴሌብር ተጠቃሚ ደንበኞች ቁጥርም 41 ሚሊዮን መድረሱን አስታወቀ።

ኢትዮ ቴሌኮም የ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ መንፈቀ ዓመት የሥራ አፈጻጸም በቀረበበት ወቅት ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ ፍሬህይወት ታምሩ እንደተናገሩት፤ በአሁኑ ጊዜ ኢትዮ ቴሌኮም የደንበኞችን ቁጥር 74 ነጥብ 6 ሚሊዮን ማድረስ ችሏል። እድገቱም ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የአራት ነጥብ ሰባት በመቶ እድገት የተመዘገበበት ነው።

ውጤቱም ለመጀመሪያ ጊዜ ከሌላ ተቋም ጋር ውድድር ውስጥ በመግባት የተገኘ መሆኑን ገልጸው፤ ተቋሙ በአሁኑ ወቅት በዓለም ካሉ 774 ኦፕሬተሮች 19ኛ እንዲሁም በአፍሪካ ካሉ 195 ኦፕሬተሮች ደግሞ ሁለተኛ ደረጃ ለመያዝ መብቃቱን ተናግረዋል።

በተመሳሳይ ተቋሙ የቴሌ ብር አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቁጥር በመጨመር ረገድም ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ባለፉት ስድስት ወራት ከ 41 ሚሊዮን በላይ የቴሌ ብር ተጠቃሚ ደንበኞችን ማፍራት እንደተቻለ አመልክተዋል።

የግብይት መጠኑንም 910 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር

ኢትዮ ቴሌኮም... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ፎቶ፡ ገበበ ገብሬ

ፍሬህይወት ታምሩ









አቶ አብደላ ነጋሽ

## ለውጭ ገበያ ከተላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከ298 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኘ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ለውጭ ገበያ ከተላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ከ298 ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የግብርና ሚኒስቴር የሆርቲካልቸር ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብደላ ነጋሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ለውጭ ገበያ ከተላኩት የሆርቲካልቸር ሰብሎች 298 ሚሊዮን 794ሺ ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት ተችሏል።

ለውጭ ገበያ ከተላኩት የሆርቲካልቸር ምርቶች መካከል 29 ሺህ 288 ቶን በላዩ የእንሰትና ሥራሥር ምርት መሆኑን አመላክተዋል።

በተጨማሪ 46 ሺህ 984 ቶን በላይ የአበባ፣ 21 ሺህ 276 ቶን በላይ የፍራፍሬና 74 ሺህ 336 ቶን በላይ የአትክልትና እጣን ምርቶችን መላክ መቻሉን ገልጸዋል።

ወደ ውጭ ገበያ የተላኩት ምርቶች ከ2015 በጀት ዓመት ከተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ከታቀደው በላይ መሆኑን አንስተው፤ የውጭ ምንዛሪ ከማስገኘት አንጻር ግን ዝቅተኛ ገቢ የተገኘ መገኘቱን አመላክተዋል።

በተለይም ወደ ውጭ የተላኩት የእንሰትና ሥራሥር ምርቶች እንዲሁም የአበባ ምርቶች መቀነሳቸውን ጠቁመው፤ ገቢያቸውም በዚያው ልክ መቀነሱን አስታውቀዋል።

የገቢውን መቀነስ ምክንያት ለማጥናት ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር በጋራ ጥናቶችን በማካሄድ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ለማምጣት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

አቶ አብደላ እንዳመላከቱት፤ ምርቶቹ የሚላኩባቸው በርካታ የገበያ መዳረሻዎች አሉ። የአበባ ምርት ቀዳሚዋ የገበያ መዳረሻ ኔዘርላንድ ስትሆን በሌሎችም ለአውሮፓ ሀገራት ገበያ ይቀርባል።

የእንሰትና የሥራሥር ምርቶችን ከምሥራቅ አፍሪካ እስከ መካከለኛው ምሥራቅ ባሉ ሀገራት እየተላኩ መሆኑን ገልጸዋል።

የሆርቲካልቸር ዘርፉ እንደሀገር ካለው አቅም አንጻር እስካሁን እያስገኘ ያለው የውጭ ምንዛሪ እምብዛም አይደለም ያሉት አቶ አብደላ፤ ይህም በሆርቲካልቸር ምርቶች ላይ ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚገባ ያሳያል ብለዋል።

በቀጣይ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ በፖሊሲና በስትራቴጂዎች በመደገፍ የተሻለ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ሥራዎች መስራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

# የግብርና ተኪ ምርቶች ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ

**አዲሱ ገረመው**



በግብርና ውስጥ በመሠረተ ልማት፣ በምርምርና በቴክኖሎጂ ኢንቨስት በማድረግ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ የግብርና ምርቶችን ሊተኩ የሚችሉ የሰብል ምርቶችን ማሳደግ እንደሚገባ ይነገራል። ከሀገራዊ ለውጡ ወዲህ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ፖሊሲዋ ላይ ለውጥ በማምጣት መንግሥት ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ጥገኝነት ለመቀነስ እየሰራ ይገኛል። በግብርና ተኪ ምርቶች ላይ ትኩረት ማድረግ በምጣኔ ሀብት ዘርፍ ትልቅ ሀገራዊ ፋይዳ እንዳለውም ምሁራን ይናገራሉ።

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የግብርና ኢኮኖሚክስ ተመራማሪ ቶለሳ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉት፤ በሀገር ውስጥ ማምረት አቅምን ያሳድጋል። በሀገር ውስጥ በስፋት የመተካት ሥራ ትኩረት ከተሰጣቸው የግብርና ምርቶች ውስጥ አንዱ ስንዴ ነው። ይህ እንደ ሀገር በከፍተኛ ደረጃ እየተሠራ ይገኛል።

ከዚህ ቀደም ስንዴ በአብዛኛው የሚመጣው ከውጪ ሀገር ነበር። የቢራ ገብስና ሌሎች የግብርና ውጤቶችም በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጪ ነው የሚገቡት። የሀገር ውስጥ አቅሙ እያለ ለሌሎች ሀገራዊ ዓላማ መዋል ያለበት ሀብትም ለእነዚህ ምርቶች ይውል ነበር ሲሉ ያስረዳሉ።

ከውጪ የሚመጣውን ምርት በሀገር ውስጥ መተካት ትልቅ አቅም መሆኑን የሚናገሩት ተመራማሪው፤ ‹‹ራስን ለመቻል እንዲሁም ምርት ከውጪ ለማስገባት የሚወጣው የውጪ ምንዛሬ ለሌሎች ወሳኝ ሥራዎች እንዲውል ያደርጋል›› ይላሉ።

የሀገር ውስጥ ምርትን በማሳደግ በተለይ በግብርና ምርት ራስን በራስ መቻል ትልቅ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ከስንዴ ውጪ ባሉት ሁሉም ዘርፎች ሊሠራበት እንደሚገባ ይመክራሉ። እንደ ሀገር በግብርና ምርት ራስን የመቻል ደረጃ ላይ ቢደረስ ለሀገሪቷ የኢኮኖሚ ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ስላለው በከፍተኛ ደረጃ ሊሰራበት እንደሚገባ ይጠቅሳሉ።

ተማራማሪው እንደሚሉት፤ ራስን ለመቻል፣ ከጥገኝነት ለመላቀቅ ችግርን በራስ አቅም መፍታት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን በዓለም በተለያዩ ማዕዘናት የሚስተዋሉ የጸጥታ ችግሮች፤ የዓለም ገበያ የዋጋ ንረት ከፍ እያለ በሚሄድበት ወቅት አቅርቦቱ ላይ ትልቅ ችግር ይፈጥራል። ራስን ከመቻል የተሻለ አማራጭ ባለመኖሩ ሁሉም ባለድርሻ አካል በተለይ የግብርና ተኪ ምርቶች እንዲስፋፉ በትኩረት ሊሰሩ ይገባል።

የጋምቤላ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ የግብርና ሜካናይዜሽንና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ኡጉታ ኡኩኝ፤ እንደ ሀገር በተለይ ከለውጡ ወዲህ ተኪ ምርቶች ላይ የተጀመሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ያነሳሉ። የግብርና ተኪ ምርቶች ላይ እያንዳንዱ ክልል በከፍተኛ ሁኔታ እየሰራበት መሆኑንም ይጠቅሳሉ።

ከዋና ዋና ሰብሎች መካከል እንደ ስንዴ፣ ሩዝ፣ አኩሪ አተር የመሳሰሉትን በስፋት ማልማት የተለመደ አልነበረም የሚሉት አቶ ኡጉታ፤ በአሁን ወቅት ግን ሀገራዊ ዓላማን ለማሳካት በስፋት እየተተገበረ እንዳለ ያመላክታሉ።

በብዛት ለማምረት ትራክተሮች ተሰማርተው የመስኖ አውታሮችና የመሬት ዝግጅት ተደርጎ የሀገርን ገጽታ ሊለውጥ በሚችል መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ይጠቁማሉ። በተለይ ከአረንጓዴ ልማት ጋር በተያያዘ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው እንደ አቡካዶ፣ ፓፓያ፣ ሙዝና ሌሎች የፍራፍሬ ምርቶች በስፋት መልማታቸውን ይጠቅሳሉ።

ተኪ ምርቶችን በስፋት ማምረት አርሶአደሩ ብቻ ሳይሆን ባለሀብቱ ከልማት ባንክ ብድር ወስዶ ግብርናው ላይ መዋዕለ ንዋዩን በማስፍሰስ እየሰራ መሆኑን በማንሳት፤ ተኪ ምርቶችን የሀገር ውስጥ የምግብ ፍጆታ ከመሸፈን ባሻገር ወደ ውጪ እየላኩ መሆናቸውንም ይገልጻሉ። ይህ በውጪ ምንዛሬ በኩል ይስተዋል የነበረውን ችግር ለመፍታት አንዱ መፍትሄ መሆኑንም ይናገራሉ።

እንደ አቶ ኡጉታ ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም ባለሀብቱ በስፋት የሚሳተፈው የኢንዱስትሪ ምርቶች ላይ ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወደህ ግን ዋና ዋና ሰብሎችን የማምረት ዝንባሌያቸው ጎልቶ እየታየ ነው። በቆሎ፣ ሰሊጥ፣ ማሾ፣ አኩሪ አተርና መሰል ነባር ዝርያ ያላቸውን ምርቶች እያመረቱ ለገበያ እያቀረቡ ነው። ይህ እየናረ ያለውን የገበያ ዋጋ ለማረጋጋት ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

“ሁሉም አርሶአደሮች እኩል አያመርቱም። ገበያ መር የሆኑ አርሶ አደሮች አሉ። መሬት ኖሮ ምርት በስፋት ማምረት የማይችሉም አሉ” በማለት ባለሀብቱ በዚህ ዘርፍ መሰማራቱ የምግብ ዋስትናን ይበልጥ ለማረጋገጥ እንደሚረዳ ይገልጻሉ።

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ ዞን ግብርና መምሪያ ኃላፊ አቶ ባንኬ ሱሜ በበኩላቸው፤ በክልሎች ትልቅ አቅም ያላቸው ወንዞች መጠቀም ቢቻል ለተኪ የሰብል ልማት ትልቅ አቅም መፍጠር እንደሚቻል በመጥቀስ፤ ይህንን ማድረግ ባለመቻሉ ለብዙ ዓመታት አንዳንድ ምርቶች ከውጪ ሲገቡ እንደነበር ያስታውሳሉ። በሀገሪቷ ሰፊ ለም መሬትና ለግብርናው ምቹ የሆነ ሥነ ምህዳር እያለ እንደሀገር ከውጪ ምርት ማስገባት ኪሳራ መሆኑን ይገልጻሉ።

ኢትዮጵያ ምርትን ከማስገባት ይልቅ በብዛት መላክ የነበረባት ሀገር ናት የሚሉት አቶ ባንኬ፤ በአሁኑ ወቅት ከውጪ የሚገቡትን ምርቶች ለመተካት እንደ ሀገር በግብርና ሚኒስቴር በሚቀመጡ አቅጣጫዎች እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ተጨባጭ ውጤት እያመጡ መሆናቸውን ያነሳሉ።

ከውጪ የሚገባውን ምርት መተካት ማለት ምርት ለማስገባት የሚወጣውን ዶላር መተካት ማለት እንደሆነ በመግለጽ፤ ሙሉ አቅምን ተጠቅሞ ማምረት እንደ ሀገር ራስን በምግብ ለመቻል እንደሚያግዝ ይናገራሉ።

“ዶላር በማውጣት ከውጪ ሰብል ከማስገባት ሰብል አምርቶ ወደ ውጪ በመላክ ዶላር መግዛት ለሀገር ኢኮኖሚ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው ነው። እንደ ታዳጊ ሀገር አዋጭ መንገድ ይህ ነው” በማለት ያስረዳሉ።

ባለሙያዎቹ በአሁኑ ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የዋጋ ንረቱ እየጨመረና ጦርነቶችም እየተስፋፉ በመሆኑ ዘርፈ ብዙ ችግሮች እየመጡ ነው። ከውጪ የሚገቡ ነገሮች ላይ እጥረት እየተከሰተ በመሆኑ ከዚህ ሁሉ ጫና ለመውጣት በተቻለ መጠን ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት ያስፈልጋል።

# የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መድረክ ለሰላምና ለሀገር ግንባታ መጠናከር አስተዋጽኦ ያደርጋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የንቅናቄ መድረክ ለሰላምና ለሀገር ግንባታ መጠናከር ጉልህ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት የሰላም ሚኒስቴርና ትምህርት ሚኒስቴር ገለጹ።

“ዓድዋን ለጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ” በሚል መሪ ቃል በሰላም ሚኒስቴርና በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰላምና ሀገር ግንባታ የንቅናቄ መድረክ እስከ የካቲት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ይካሄዳል።

በሰላም ሚኒስቴር የሰላም ግንባታና ብሔራዊ መግባባት ሚኒስትር ዴኤታ ከይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ በሀገሪቱ የሚገኙ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመማር ማስተማር ተግባራቸው ጎን ለጎን በሰላም ጉዳይ ያላቸው ድርሻ የጎላ በመሆኑ በንቅናቄው በሀገራዊ ማንነት፣ እሴትና ጥቅም ዙሪያ ውይይቶች ይካሄዳል።

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሄደው የንቅናቄ መድረክ ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ግብዓት መሆን የሚችል ሃሳብ ይገኝበታል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በመድረኩ ዓድዋን ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ለማዋል የሚያስችሉ የመወያያ ሰነዶች እንደሚቀርቡም ገልጸዋል።

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሀገራዊ አንድነትን ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን የጠቆሙት ከይረዲን /ዶ/ር/፤ የተዘጋጁት የመወያያ ሰነዶች ከዓደዋ ድል ጋር



ከይረዲን ተዘራ/ዶ/ር/

የተሳሰሩ ናቸው ብለዋል።

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሀገራዊ መንግሥት ግንባታ ድርሻቸው ትልቅ መሆኑንም ጠቅሰው፤ ንቅናቄው የሀገራዊ መንግሥት ግንባታን በጠንካራ መሠረት ላይ ለማስቀመጥ እንደሚያስችል ተናግረዋል።

ሀገራዊ ንቅናቄው በሁሉም የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሄድ መሆኑን ገልጸው፤ ሀገረ መንግሥትን በጠንካራ መሰረት ላይ ለመጣል የሚደረገውን ጥረት የሚደግፍ መሆኑን ገልጸዋል።

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ልማት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ኮራ ጡሹኔ በበኩላቸው፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከተለያዩ ከሀገሪቱ ክፍል የሚመጡ ኢትዮጵያውያን የያዙ በመሆናቸው በንቅናቄው የተለያዩ ሃሳቦች ተነስተው ገንቢ ውይይት ይደረጋል ብለዋል።

ተቋማቱ የግጭት አጀንዳዎች መዳረሻ በመሆን የተለያዩ ችግሮች ሲከሰቱ ቆይተዋል ያሉት አቶ ኩራ፤ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚነጋገር፣ የሚወያይ፣ ኃላፊነትን የሚወስድ ማህበረሰብን መፍጠር ያስፈልጋል ሲሉ ጠቁመዋል።

በዘላቂነት ዩኒቨርሲቲዎችን የሰላም ምንጭ ለማድረግ ከሰላም ሚኒስቴር ጋር በመሆን እየተሠራ መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም በተቋማቱ ሰላምን የሚያጎለብትና የሚያጠናክር እንቅስቃሴ እንደሚደረግ አመላክተዋል።

ዓደዋ ኢትዮጵያውያን በጋራ ቢቆሙ ድል ማድረግ እንደሚችሉ የታየበት በመሆኑ በዓድዋ የታየውን አንድነት በመጠቀም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ሰላም ማጎልበት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

እንደሀገር የዓድዋን እሴትና አዎንታዊ ታሪኮችን በማጎልበት ወደ ማህበረሰቡ ማምጣት እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ንቅናቄው ሰላማዊ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ለመፍጠርና ሀገረ መንግሥትን ለመገንባት እንደሚረዳ ተናግረዋል።

በሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሄደው የንቅናቄ መድረኩ እስከ የካቲት 21 ቀን 2016 ዓ.ም ይቀጥላል። በማጠቃለያ ቀኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ የመዝጊያ መርሀ ግብር እንደሚኖረው ተገልጿል።



ወይዘሮ አሰገድ ምሬሳ

## የታብሌት ስርጭቱ የመምህራንን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅም ያጎለብታል

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- የታብሌት ስርጭቱ የመምህራንን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅም የሚያሳድግ መሆኑን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

ትምህርት ሚኒስቴር የመምህራንና ትምህርት ቤት አመራሮችን የቴክኖሎጂ ክህሎት በማሻሻል የመማር ማስተማር ሂደቱን በዲጂታል ቴክኖሎጂ መደገፍን ዓላማ ያደረገ የታብሌት ስርጭት በትናንትናው እለት አካሂዷል፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራንና ትምህርት አመራር ልማትና አስተዳደር ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አሰገድ ምሬሳ እንደገለጹት ፤ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ከዓለም ጋር አብሮ ለመሄድ የትምህርት ሥርዓቱን በቴክኖሎጂ መደገፍ ያስፈልጋል።ለዚህም መምህራን ስለ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በቂ እውቀት ሊኖራቸው እንደሚገባ በመታመኑ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለሁለት ዓመታት እቅድ ነድፎ እየሰራ ይገኛል።

ትምህርት ሚኒስቴር ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ሲሰራ የቆየ መሆኑን ገልጸው፤ በ 2016 ዓ.ም መምህራንን በቴክኖሎጂ ብቁ ለማድረግ የሶስት ሺህ 790 ታብሌቶችን ግዢ በመፈጸም ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች አሰራጭቷል ብለዋል።

ወይዘሮ አሰገድ የታብሌት ስርጭቱ የመምህራንን እና የትምህርት ቤት የአመራሮችን የዲጂታል ቴክኖሎጂ ክህሎት አቅም ማሳደግን ዓላማ ያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ የመምህራንና የአመራሮች ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ አቅም በመገንባት በትምህርት ተቋማት የሚሰጠውን የመማር ማስተማር ጥራት ለማሻሻል ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አስገንዝበዋል።

የታብሌቶቹ ግዢ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን የዲጂታል ክህሎት በማሻሻል የመማር ማስተማር ተግባርን በቴክኖሎጂ እንዲሰጡ ከማስቻል በተጨማሪ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራንና አመራሮች አጫጭር የሥራ ላይ ስልጠናዎች በዲጂታል ቴክኖሎጂ እንዲያገኙ ያስችላል ብለዋል።

ታብሌቶቹ በጦርነት ለተጎዱ አካባቢዎችና በትምህርት ጥራት ክፍተት አለባቸው ለሚባሉ አካባቢዎች እንደሚሰራጩ አመልክተው፤ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች በኩል18ሺ ለሚሆኑ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

ኃላፊዋ እንደ ሀገር ካለው የአጠቃላይ መምህራንና አመራሮች እንዲሁም ትምህርት ቤቶች ብዛት አንጻር ሲታይ የሚሰራጨው ታብሌቶች ቁጥር ጥቂት ቢሆንም የትምህርት ሥርዓቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል ተብሎ እንደሚታመን ተናግረዋል።

ታብሌቶቹ ለታለመለት ዓላማና ተግባር ብቻ እንዲውሉ ቁጥጥር ይደረጋል ብለዋል።

# በመዲናዋ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ የሚያራዝሙ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ማራዘም የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸውን የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ።

በአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ማስፋፋት ዳይሬክተር አቶ ሳምሶን አይናቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ቱሪስቶች የመዲናዋን የቱሪዝም መስህቦችና መዳረሻዎች እንዲጎበኙ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል።


በከተማዋ ፓርኮች፣ አደባባዮች ፣ሙዚየሞችና ተጨማሪ ማራኪ የመስህብ ቦታዎች እንዲለሙ በመደረጉ አዲስ አበባ የጎብኚዎችን ቀልብ በመሳብ ገቢ መፍጠር ችላለች ሲሉ ተናግረዋል።

የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ለትምህርትና ለጤና አገልግሎት፣ ለምርምር እንዲመጡ ለማድረግ ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎችንና የመዝናኛ ተቋማት፣ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን ማካሄድ የሚያስችሉ ሁለገብ አዳራሾች መሠራታቸውንና እየተሰሩም እንደሚገኙ አቶ ሳምሶን ተናግረዋል፡፡

በቅርብ ዓመታት የተገነቡት የቱሪዝም መዳረሻዎች ከገቢ ምንጭነት ባሻገር የከተማዋ የውበት መገለጫ መሆናቸውንም ጠቁመው፤ ይህም ጎብኚዎችን ለመሳብና የቆይታ ጊዜያቸውን ለማራዘም ይረዳል ብለዋል።

አዲስ አበባ የበርካታ አብያተ ክርስቲያናት፣ ጥንታዊ መኖሪያ ቤቶችና ሕንፃዎች፣ ሐውልቶች ያሉባት ከተማ መሆኗን አንስተው፤ ይህ በራሱ ጎብኚዎች አማራጮች እንዲኖሯቸው ያስቻለ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በመዲናዋ ሰፊ የቱሪዝም አቅም ያላቸው የአንድነትና የእንጦጦ ፓርኮች፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ የሳይንስ ሙዚየም፣ የአዲስ አበባ ፓርክ እንዲሁም ሌሎች የቱሪዝም መስህቦችና መዳረሻዎች መኖራቸው ለጎብኚዎች ጥንታዊውን መስህብ ከአሁናዊ ገፅታ ጋር አስተሳስሮ ለመመልከት እንደሚረዳ አብራርተዋል፡፡



እንደ አቶ ሳምሶን ገለፃ፤ የከተማ አስተዳደሩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን ለመሳብና የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚን ለማሳደግ ተከታታይ የልማት ሥራዎችን ሰርቷል።

ከተማዋ የግንኙነትን አስፈላጊነት በመገንዘብ ቦታዎችን የማስፋፋትና የማዘመን እንዲሁም በመሰረተ ልማት ዝርጋታ ላይ ኢንቨስት በማድረግ ላይ ትገኛለች ብለዋል። ይህ ማሻሻያ የከተማዋን ከፍተኛ የቱሪስት መዳረሻዎችን የማስተናገድ አቅም ያሳድጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ቢሮው ከቱሪዝም ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የከተማዋን ባህላዊ ቅርሶች፣ ታሪካዊ ቦታዎች እና የከተማዋን ገጽታ ለማስተዋወቅ ሁሉን አቀፍ ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል ያሉት አቶ ሳምሶን፤ የጎብኚዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የጤናና የንጽህና ፕሮቶኮሎችን በሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና የቱሪስት መስህቦች ላይ በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አንስተዋል። ይህም አዲስ አበባ ለመዝናኛ፣ ለቢዝነስ እና ለባህል ቱሪዝም ዋና መዳረሻ እንድትሆን ያደርጋታል ብለዋል።

በአዲስ አበባ ያለው የቱሪዝም መነቃቃት ለሥራ እድል ፈጠራ እና ለድህነት ቅነሳ አንዱ መፍትሄ ነው ያሉት አቶ ሳምሶን፤ የከተማዋ ታሪካዊ ምልክቶች እንደ ዓድዋ ዜሮ ዜሮ ሙዚየም፣ ባህላዊ ዝግጅቶች እና ሞቅ ያለ መስተንግዶ ከመላው ዓለም የሚመጡ ተጓዦችን በማሳመን ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ አመላክተዋል።

# የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማሳደግ እየተሰራ ነው

## - በኦሮሚያ የአርብቶ አደሮች ቀን ተከበረ

ገመቹ ከድር

አዳማ፡- የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃመሚነት ለማሳደግ እየሰራ መሆኑን የኦሮሚያ ክልል አስታወቀ።

የኦሮሚያ መስኖና አርብቶ አደር ቢሮ 19ኛው የኦሮሚያ አርብቶ አደሮች ቀንን "የአርብቶ አደር ልማት ለጋራ ብልፅግና " በሚል መሪ ሃሳብ አዳማ ከተማ አክብሯል።

በኦሮሚያ ክልል ምክትል ፕሬዚዳንት ማዕረግ የገጠር ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱራህማን አብደላ በዓሉ ላይ እንደገለጹት ፤ አርብቶ አደርነት ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር ለሠላም፣ለባህላዊና ማህበራዊ መስተጋብር ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ለዘመናት ትኩረት ያልተሰጠውን የአርብቶ አደሩን ሕይወት በሚፈለገው ልክ ለማሸጋገር ከለውጡ ወዲህ መንግሥት የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን በማውጣት እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

በተለይም በ10 ቢሊዮን ብር ወጪ የ"ፍና" ፕሮጀክት ግንባታን በማከናወን የአርብቶ አደሩንና የእንስሳት የመጠጥ ውሃ ፣ግጦሾች እጥረት ለመፍታት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

የአርብቶ አደሩን መሠረተ ልማት ችግሮችን በዘላቂነት የሚፈቱ የጤናና ትምህርት ተቋማት ግንባታ እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ የመንገድ ግንባታ እየተካሄዱ ይገኛል ብለዋል።

አርብቶ አደሩ በቴክኖሎጂ በመታገዝ የእንስሳት እርባታ ጥራትንና ምርትና ምርታማነትን በመጨመር ረገድ ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ የቁጠባ ባህልን በማሳደግ ለተሻለ ለውጥ እንዲበቁ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል። የገዳ ሥርዓትን ጠብቆ ለትውልድ በማስተላለፍ ረገድ አርብቶ አደሮች ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።



የኦሮሚያ መስኖና አርብቶ አደር ልማት ቢሮ ኃላፊ ግርማ ረጋሣ (ኢ/ር) በበኩላቸው፤ አምስት ሚሊዮን አርብቶ አደር ክልሉ ካለው የቆዳ ስፋት ላይ 43 በመቶ በሚሆነው ላይ ሰፍሮ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

እንደ ሀገር በሚደረገው ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከ12 እስከ 16 በመቶ የእንስሳት ሀብት በማቅረብ አርብቶ አደሮች አስተዋፅኦ አላቸው ያሉት ኃላፊው፤ የአርብቶ አደሩን የውሃ እጥረት ፣የእንስሳት ግጦሽና የገበያ ትስስር ችግሮችን ለመፍታት የክልሉ መንግስት በትኩረት እየሰራ መሆኑን አመላክተዋል።

በኦሮሚያ ክልል የቦረና ዞን መስኖና አርብቶ አደር ልማት ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ታዲ ገርብቻ በበኩላቸው፤ ለአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ በመንግሥት የተሰጠው ትኩረት አበረታች ውጤት እያመጣ ይገኛል ብለዋል።

በዞኑ የአርብቶ አደሩን ችግር የሚፈቱ ፕሮጀክቶች ተገንብተው በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸውን ጠቁመው፤ እስከ አሁን በተሰራው ሥራ ስምንት የውሃ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ለህብረተሰቡ አገልግሎት መስጠት መጀመራቸውን ገልጸዋል።

በቦረና ዞን ገሞሌ ወረዳ ሞዴል አርብቶ አደር የሆኑ አቶ ጎፊሬ ቁሪ ለአርብቶ አደሩ ህብረተሰብ እየተደረገ ያለው ድጋፍ ሕይወታችንን በመቀየር ላይ ይገኛል ብለዋል።

ፍና ፕሮጀክት ለሰውና ለእንስሳት መጠጥ እንዲሁም ለመስኖ እርሻ ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ላይ መሆኑን ተናግረው፤ እሳቸውም 100 ግመሎች ፣250 ቀንድ ከብቶችና 400 ፍየሎችን በአጠቃላይ ያላቸው ንብረት 94 ሚሊዮን ካፒታል በማፍራት ሞደል አርብቶ አደር በመሆን በመሸለማቸው ለበለጠ ሥራ እንደሚያነሳሳቸው አስታውቀዋል።

በዓሉ የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች፣ የክልሉ አርብቶ አደር ተወካዮች፣ ባለድርሻ አካላትና ምሁራን በተገኙበት በተለያዩ ፕሮግራሞች ተከብሯል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፎረሙ መመስረት ዳያስፖራው ለሀገሩ እድገት የአቅሙን እንዲያበረክት የሚረዳው ነው!

በተለያዩ ምክንያቶች ከትውልድ ሀገራቸው ወጥተው በሌላ ሀገር ለመኖር የተገደዱ የአንድ ሀገር ዜጎች /ዳያስፖራዎች ለሀገራቸው እና ለህዝባቸው ካላቸው ፅኑ ፍቅር የተነሳ ስለ ሀገራቸው ብዙ ዋጋ የሚከፍሉበት ሁኔታ የተለመደ ነው። ለሀገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው።

በተለይም በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገራት ዳያስፖራዎች በሚኖሩባቸው ሀገራት ሆነው የሀገሮቻቸውን እና ህዝቦቻቸውን ህይወት ለመቀየር በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ዋነኛ ተዋንያን ሆነው ማየት የተለመደ ነው፤ በዚህም ውጤታማ በመሆን በሀገራቸው እድገት ውስጥ አሻራቸውን በስፋት ማሳረፍ ችለዋል።

እነዚህ ዳያስፖራዎች ለሀገራቸው በጎ ከማሰብ ጀምሮ በገንዘባቸውና በእውቀታቸው ለሀገራቸው እና ለህዝባቸው ነገዎች የሚቻላቸውን ሁሉ በማድረግ ፤ ለህዝባቸው ያላቸውን አጋርነት በተጨባጭ በማሳየት በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እያተረፉ ያለበት እውነታም ሰፊ ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ ህንድና ፊሊፒንስ ያሉ ሀገራት ተጠቃሽ ናቸው።

በኛም ሀገር ያለው እውነታ ቡራቡሬ መልክ ቢኖረውም፤ አብዛኛው የዳያስፖራ ማህበረሰብ በኢትዮጵያዊ ጨዋነት እና የሀገር ፍቅር ለሀገሩና ለወገኑ ባለው አቅም ሁሉ የተቻለውን ለማድረግ የሚጥር ነው። በዚህም፤ በተለይም ሀገሪቱ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በምትገኝበት ሁኔታም ሆነ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የነበረው እና ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

ይህም ሆኖ ግን ዳያስፖራው ማህበረሰብ ካለው ሁለንተናዊ አቅም አንጻር፤ እስካሁን ያለው ሀገራዊ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተሳጥፎ በቂ ነው የሚባል አይደለም። በተለይም በኢኮኖሚው ዘርፍ ሀገሪቱ ያሏትን ጸጋዎች ለማልማት የሚያስፈልጋትን ሀብት በማፈላለግ ሆነ የሀብት ምንጭ በመሆን በሚጠበቀው መልኩ እየተንቀሳቀሰ አይደለም።

ከዚህም ባለፈ በሀገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ ዘመን በሚዋጅ የፖለቲካ አስተሳሰብ ተሳታፊ በመሆን፤ ሀገር አሻጋሪ የለውጥ አስተሳሰቦች በማህበረሰብ ውስጥ ጉልበት አግኝተው ፤ሀገር እንደ ሀገር ወደተሻለ የፖለቲካ ምእራፍ የምትሸጋገርበትን እድሎች በመፍጠርም ሆነ የተፈጠሩትን በማጎልበት ሂደት ውስጥ ውስንነቶች ይታዩበታል።

በማህበራዊ ሆነ በቴክኖሎጂ ዘርፎችም ቢሆን፤ ዳያስፖራው ሀገርን ሊጠቅም የሚችል የዳበረ እውቀትና ክህሎት ባለቤት ቢሆንም፤ በተለያዩ ምክንያቶች ይህንን አቅም በተደራጀ መንገድ ለሀገር ልማት፤ ለዜጎች ማህበራዊ እድገት በመጠቀም ሂደት በተመሳሳይ መልኩ ሰፊ ክፍተት የሚታይበት ነው።

በአጠቃላይ እስካሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ ዲያስፖራው በሀገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በተደራጀ መንገድ የሚጠበቀውን ያህል አዎንታዊ ተሳትፎ እያደረገ አይደለም፤የዚህን ኃይል አቅም በአግባቡ ለመጠቀም ሰፊ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

በተለይም ዳያስፖራው ማህበረሰብ ስለሀገሩና በሀገሩ እየተካሄዱ ስላሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጦች ተገቢም መረጃ እንዲያገኝ በማድረግ፤ ከውዥንብሮች ነጻ ሆኖ የለውጡ አካል እንዲሆን በስፋት መንቀሳቀስ ፤ ለዚህ የሚሆን ዝግጁነት መፍጠር ያስፈልጋል።

ዳያስፖራው ማህበረሰብ በራሱ ተነሳሽነት በየዘርፉ ያለውን አቅም አቀናጅቶ ፣ለሀገሩና ለወገኑ አቅም የሚሆንበትን ሁኔታ መፍጠርም አስፈላጊ ነው። ከዚህ አንጻር ሰሞኑን ዳያስፖራው ባለው አቅም ስለ ሀገሩ የሚቻለውን ሁሉ እንዲያበረክት፤ የዳያስፖራ ዲፕሎማሲ አማካሪ ፎረም መመስረቱ እንደ ትልቅ ስኬት ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ፎረሙ ዳያስፖራው ማህበረሰብ ሀገራችን አሁን ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያጋጠሟት ያሉትን ጫናዎች ለመቋቋምም ሆነ በቀጣይ ሊያጋጥሟት የሚችሉትን ተግዳሮቶች ሰብሮ ለመውጣት ተጨማሪ አቅም ሊሆን የሚችልበትን እድል የሚፈጥርበት እንደሆነም ይታመናል።

በተለይም ሀገር ብሄራዊ ጥቅሞችን መሰረት ባደረጉ ንቅናቄዎች ውስጥ የዳያስፖራውን ሁለንተናዊ አቅምና ተሳትፎ በምትፈልግበት አሁናዊ ሁኔታ ፎረሙ መመስረቱ፤ ዲያስፖራው ማህበረሰብ በዘርፉ ያለውን አቅም ለሀገሩ ብሩህ ነገዎች በተሻለ መንገድ እንዲያውል ይረዳዋል።

መንግሥት የሁላችንም ሀገር በሆነችው በኢትዮጵያ ጉዳይ በመነጋገርና በመግባባት ለሁለንተናዊ ዕድገቷ አብረን እንስራ፤ ለትውልዶች አመቺ የሆነች ሀገር እንገንባ በሚል ተደጋጋሚ ጥሪዎችን እያደረገች ባለበት ወቅት የፎረሙ መመስረት፤ዲያስፖራው ለሀገሪቱ እድገት የሚኖረውን ስትራቴጂካዊ አስተዋፅኦ የሚያሳድግ ነው፤የራሱን ታሪክ እንዲሰራም መልካም እድል የሚፈጥርለት ነው።

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በባህር በር ጉዳይ ሁሉም ዜጋ በኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀስ ይገባል

አስመረት ብስራት

የሰሞኑ ትልቁ ሀገራዊ አጀንዳችን የባህር በር ይኑረን አይኑረን የሚል መሆኑን ብናገር ለቀባሪው አረዱት ይሆንብኛል። ነገር ግን የባህር በር ጥያቄ ጦርነት ሊያስነሳ ይችል ይሆን የሚል ስጋት በአብዛኞቻችን ዘንድ እንደነበር ይታወሳል። ስጋቱ እውነት መሰረት አለው? ወይስ መሰረተ ቢስ? የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በዓለምአቀፍ ህጎች እይታ እንዴት ይታያሉ? የሚለውን ለመመልከት ሞከርኩ።

የባሕር በርን በተመለከተ ዓለም አቀፍ ሕጎች ፤ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በአቅራቢያቸው የሚገኝ የባህር ወደቦችን በተለያየ አመራጮች የመጠቀም መብት እንዳላቸው ይደነግጋሉ።

ለምሳሌ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባህር ሕግ አንቀጽ 69 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 5 ያለው ላይ እንደሰፈረው፤ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ካለው ባህር የተፈጥሮ ሀብት እኩል የመጠቀም መብት አላቸው።ዓሳ ማጥመድን፣ በባህር ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሀብቶችን ፍለጋ ጨምሮ ሌሎች ከባህር ተፈጥሮ ሀብት ጋር የተያያዙ ሀብቶች ተጠቃሚነት መብትን ያካትታል፡፡

በዚሁ ሕግ አንቀጽ 125 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተመለከተው ደግሞ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በአካባቢያቸው ያለውን ባህር የመጠቀም እና የመሸጋገር ዓለም አቀፍ መብት አላቸው። የባህር በር በሌለው ሀገር፣ የባህር በር ባለቤት በሆነው ሀገር እና በቀጣናው መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊፈጸም እንደሚገባ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ ተመላክቷል፡፡

አንቀጽ 27 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ደግሞ እነዚህ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት በስምምነት ከተደረገ የተለየ የአገልግሎት ክፍያ ከሌለ በስተቀር ለተገለገሉበት ባህር ምንም ዓይነት የትራፊክ ታክስ ወይንም ሌላ ክፍያ እንደማይጠየቁ ይደነግጋል፡፡

የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በምስረታ ቻርተሩ መግቢያ ላይ በባህር ሕግ ጉዳዮች ላይ ባሰፈረው ሀተታ የአፍሪካ ሀገራት የባህር በር ያላቸውን ጨምሮ ከባህር ሊያገኙት የሚገባቸውን ጥቅም እያገኙ እንዳልሆነ ጠቅሶ፣ የባህር በር የሌላቸው ሀገራት ከባህር የመጠቀም መብታቸው ሊጠበቅ እንደሚገባ እና ይህም ከዓለም አቀፍ መርህ አንጻር መታየት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ከላይ ባነሳናቸው ድንጋጌዎች መሰረት ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት መብት የላትም ትላላችሁ ? እንደኔ እንደኔ ከታሪክ፣ ከሞራል፣ ከዓለም አቀፍ ህግም አኳያ አካባቢዋ ባሉ ወደቦች የመጠቀም መብት አላት።

ኢትዮጵያ ከባህር በር ጋር ያላት ታሪካዊ ዳራ ሲታይ የጎን ስፋቱ ፤ከ50 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የማይበልጠውን እና ከመርሳ ፋጡማ ተነስቶ የትግራይን እና አፋርን ምድር እየታከከ ቁልቁል እስከ ራስ ዱሜራስ የሚወርደውን ቀጭን መሬት ያየ ሁሉ፤ የኢጣሊያ ቅኝ ገዢዎች ኢትዮጵያ ወደ ቀይ ባህር የሚያስወጣ መሬት እንዳይኖራት ሆን ብለው ያጠሩት አጥር መሆኑን መረዳት ይሳነዋል ብዬ አላስብም።

ኢትዮጵያ ይህንን አጥር አፍርሳ ኤርትራን ለመቀላቀል ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉባኤ ጥያቄ ባቀረበችበትና ሙግት ባካሄደችው የዲፕሎማሲ ዘመቻ ወቅት የባህር በር እንድታገኝ የሚያስችል መሬት ተፈቅዶላት እንደነበረ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለማርያም "አሰብ የማን ናት? (የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ)" በሚለው መጽሐፋቸው ላይ አስፍረዋል።

የኢትዮጵያ የወቅቱ ጥያቄ መላዋን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ማዋሃድ ስለነበር የተፈቀደላትን የባህር በር የማግኘት አማራጭ አልተቀበለችውም ነበር። ክርክሩ እና የዲፕሎማሲው ዘመቻ ፍሬ አፍርቶ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን እንድትቀላቀል ተወስኖ ኢትዮጵያም ዳግም የባህር በር መሆኗ ይታወቃል።

እንደ ዶክተር ያዕቆብ ኃይለ ማርያም ፤በወቅቱ የነበሩት መንግሥታት በፌዴሬሽኑ አያያዝ ላይ በተከታታይ በፈፀሟቸው ስህተቶች ፌዴሬሽኑ ፈርሶ ጦርነት ተካሄደ።በጦርነቱም ብዙ ደም መፋሰስ እንደነበር ታሪክ ያስረዳል።ኤርትራ ነጻ ሀገር እንድትሆን በተፈቀደበት ወቅትም ኢትዮጵያ ሕጋዊ የባህር በር ባለቤትነቷን እንዳታቀርብ በወቅቱ የነበሩት መሪዎቿ ተቃውመው ባዶ እጇን እንድትቀር አደረጓት፡፡

በኢትዮጵያ ሀገራዊ ለውጥ ከተደረገ ጀምሮ በትኩረት እየተሰራባቸውና ለውጥ እየመጣባቸው ካሉ ጉዳዮች አንዱ የባህር በር ጥያቄ ነው።መንግሥት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባህር በር ጥያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል

በኢትዮጵያ ሀገራዊ ለውጥ ከተደረገ ጀምሮ በትኩረት እየተሰራባቸውና ለውጥ እየመጣባቸው ካሉ ጉዳዮች አንዱ የባህር በር ጥያቄ ነው።መንግሥት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባህር በር ጥያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል።

አሁን ላይ ከብዙ ጥረት በኋላ ኢትዮጵያ ከሶስት አስርት አመታት በኋላ የባህር በር የምታገኝበት አማራጭ ተገኝቷል።ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል የቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት ሰሞኑን ከሶማሌ ላንድ ጋር የባህር በር የሚገኝበትን የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተፈራርሟል።ይህ ሲሆን፤ ታዲያ በርካታ ዜጎች በደስታ ጮቤ ረግጠዋል።የኢትጵያን ከፍታ የሚናፍቁ ወገኖችም ደስታቸውን ገልጸዋል።

በተቃራኒውም ለኢትዮጵያ በጎ የማይመኙ አንዳንድ ሀገራት እና ታሪካዊ ጠላቶቻችን ልክ የባህር ባር ልታገኝ ቀርባለች ሲባል የተቃውሞ ድምፃቸውን ማሰማት ጀመሩ። የሚያሳፍረው፤ አንዳንድ ዜጎቻችን ስምምነቱን ከሌሎቹ እኩል ሲቃወሙ መስማታቸው ነው።ይህ አሳዛኝ ታሪካዊ ክስተት በዓለም አቀፍ ደረጃም ግርምት ፈጥሯል።

የቀደሙ ታሪኮቻችን እንደሚያመለክቱት፤እንደ ሀገር ለባህር በር (ለወደብ) ብዙ መስዋእትነት ከፍለናል። የባህር በር ጉዳይ ለየትኛውም ኢትዮጵያዊ ከፖለቲካ እምነትና አስተሳሰብ በላይ ነው። ይህንን ሀገራዊ ጉዳይ አቅልሎ ማየት በየትኛውም መመዘኛ ተገቢ ያልሆነ የታሪክ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ነው።

አሁን ላይ እስከ ዛሬ በአንድም ይሁን በሌላ ምክንያት ከእጃችን የወጣውን ይህንን መብት ለመመለስ በምን መልኩ እንሂድ የሚለው ጉዳይ፤እንደ ዜጋ ዋነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳችን ሊሆን ይገባል፤ ለዚህ ጥንቃቄ የታከለበት በሳል አካሄድ ልንከተል ይገባል።ለዚህ ደግሞ ሁሉም ዜጋ በኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀስ ይገባል።

# ፍረዱኝ

# «በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ገነት ትምህርት ቤት አይዘጋም፤ ለማንም አይሰጥም»

ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር)
-የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ

ሙሉቀን ታደገ እና መክሊት ወንድወሰን

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍል ፍረዱኝ በተሰኘው አምዱ ታኅሣሥ 10 ቀን 2016 ዓ.ም «ያለ ካርታ 52 ዓመታትን የዘለቀው የገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት» በሚል ርዕስ አንድ የምርመራ ዘገባ ለሕዝብ ማቅረቡ ይታወቃል፡፡ በዚህ ዘገባ ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ቀሪ የምርመራ ዘገባዎች እንደሚኖሩ እና ቀጣይ በሚኖሩን ዝግጅቶች ከጉዳዩ ጋር የሚገናኙ የተለያዩ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እና ግለሰቦችን ይዘን እንደምንቀርብ ገልጸን ነበር፡፡

በዚህ መሠረት በዛሬው ዘገባችን ተፈጠረ ስለተባለው ችግር በአራዳ ክፍለ ከተማ የወረዳ 6 የተማሪ እና ወላጅ ኅብረት ሰብሳቢ፣ የአዲስ አባበ ትምህርት ቢሮ ኃላፊን፣ የፌዴራል ኪራይ ቤቶች ኮርፖሬሽን የሕዝብ ግንኙነት እና በፌዴራል ቤቶች ቅርንጫፍ አራት ጽሕፈት ቤት ባለሙያዎችን ምን ያውቃሉ ስንል ጠይቀናል?

## ወረዳ 6 የተማሪ እና ወላጅ ኅብረት ሰብሳቢ ምላሽ


አቶ ወንድወሰን ፍታሌ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 የተማሪ እና ወላጅ ኅብረት ሰብሳቢ ናቸው። ስለትምህርት ቤቱ ምን እንደሚያውቁ ጠይቀናቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል፡፡


ትምህርት ቤቱ በቀድሞ ከፍተኛ 13 ቀበሌ 03 ሥር የነበረ ሲሆን የ47/67 አዋጅ በታወጅ ጊዜ በመንግሥት ተወርሶ ነበር፡፡ ነገር ግን ቤቱ ሲወረስ ኪቤአድ የሚባለው ተቋም እንደሀገር አልተመሠረተም ነበር፡፡ በአዋጅ 47/67 ቤቱ ሲወረስ ያልነበረ ተቋም እንዴት አድርጎ ቤቱን ሊያገኝ ቻለ? ሲሉ ይጠይቃሉ።

እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፤ የ47/67 አዋጅ ሲታወጅ ከገነት አጻደ ሕፃናት ጋር የሚመሳሰል "ኬዝ" የነበረባቸው ትምህርት ቤቶች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ አጼ ናኦድ፣ በላይ ዘለቀ፣ አፍሪካ ኅብረት እና ሌሎችም። እነዚህ ትምህርት ቤቶች በአዋጁ ከተወረሱ በኋላ የሕዝብ ትምህርት ቤት የነበሩ ናቸው፡፡ በ2004 ዓ.ም በወጣው መመሪያ ወደ መንግሥት የዞሩበት አግባብም ከገነት ትምህርት ቤት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች አንድም ቀን ኪራይ ክፈሉ ተብለው አያውቁም፡፡ ገነት ትምህርት ቤት ግን ተለይቶ ኪራይ እንዲከፍል የሚጠየቅበት አግባብ ትክክል አለመሆኑን ይናገራሉ፡፡

ቤቶች ኮርፖሬሽን የገነት ትምህርት ቤትን ከወይዘሮ ትዝታ ዳንኤል ወረስኩት ያለው ትክክል አይመስለኝም ያሉት አቶ ወንድወሰን፣ ምክንያቱም ተወረሰ የተባለው የወይዘሮ ትዝታ ቤት ይገኛል የተባለው በቀድሞ መጠሪያው መሐል ከተማ ወረዳ 09 ነው፡፡ ነገር ግን ገነት ትምህርት ቤት ይገኝ የነበረው በከፍተኛ 13 ቀበሌ 3 ነው፡፡ ከፍተኛ 13 እና መሀል ከተማ ደግሞ መገኛቸው የተለያየ ነው። ስለዚህ ቤቶች ኮርፖሬሽን የእኔ ነው የሚለው ትምህርት ቤት የገነት ትምህርት ቤት ሳይሆን የሌላ ትምህርት ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ፡፡

ተወልጄ ያደግኩት ገነት ትምህርት ቤት አካባቢ ነው የሚሉት አቶ ወንድወሰን፤ የገነት ትምህርት ቤትን ቀበሌ 03 በጽሕፈት ቤትነት ሲጠቀምበት አይተው እንደማያውቁ እና ከመወረሱ በፊት እና በኋላም የትምህርት ቤት አገልግሎት ብቻ ሲሰጥ እንደሚያውቁት ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በ1973 ዓ.ም የቤቶች ኮርፖሬሽን ለቀበሌ 03 አከራይቶት እንደነበር የሚያትተው ሰነድ


0000007
ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT
Land Administration and Building Permit Authority
Certificate of Title Deed
№ 018454
Owner's Name
Type of building
Title deed no.
Permit No.
Lease hold
Date issue
Registration No.
COORDINATE
የፌዴራል ቤቶች የሪከርድና ማኅደር አገልግሎት ኮርፖሬሽን


የሥራና ቤት ሚኒስቴር
የቤቶች አስተዳደር ድርጅት
የመኖሪያ ቤት ማማረጫ
ውሣኔ ፡ ተፈቅዷል ፡ አልተፈቀደም ፡
አስተያየት ፡
ስም ፡ ፊርማ ፡

ፈጽሞ ስህተት መሆኑን ይገልጻሉ፡ ምናልባትም ሰነዱ ስለገነት ትምህርት ቤት ሳይሆን ስለሌላ ቦታ የሚናገር ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ፡፡

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ምላሽ

ለዝግጅት ክፍላችን አቤቱታ ያቀረቡት መምህራን እና ወላጆች እንደሚሉት የገነት ትምህርት ቤት ለ52 አመታት ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ሆኖ ቢቀጥልም የራሱ የሆነ ካርታ የለውም፡፡ በተጨማሪም በ2004 ዓ.ም የፌዴራል ቤቶች ካርታ አውጥቶበታል፡፡ ይህም ከጊዜ በኋላ ባለይዞታው ጥያቄ አቅርቦ ትምህርት ቤቱን ወደ አለመኖር ሊያመጣው ይችላል የሚል ስጋት አለባቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ ምን ይላሉ? ስንል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊን ዶክተር ዘላለም ሙላቱን ጠይቀን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

አሁን ላይ ስለገነት ትምህርት ቤት ለማውራት ጊዜው ገና ነው፡፡ ጉዳዩ ለአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮም እንደ ችግር አልተነሳለትም፡፡ ችግር ሆኖ እንኳን ቢገኝ ብዙ መፍትሔዎች አሉት፡፡ እስከዛሬ ድረስ ትምህርት ቤቱም ለቤቶች ኮርፖሬሽን ኪራይ ከፍሎ እንደማያውቅ እና እንዳልከፈለ አመላክተዋል። የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጉዳዩን በሕግ ይዞ ቢሮውን እንዳልጠየቀ ገልጸዋል፡፡

ትምህርት ቤቱ ባከናወቸው እና እያከናወናቸው ባሉት ተግባራት በኢትዮጵያ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሞዴል ተብሎ የተመረጠ መሆኑን የሚያስረዱት ኃላፊው፣ በዚህም በተማሪዎች እና በወላጆች በከፍተኛ ደረጃ ተፈላጊ መሆኑን ያስረዳሉ። በትምህርት ቢሮውም ለትምህርት ቤቱ ካለው ደረጃ አንጻር ከፍተኛ ክትትል እና ድጋፍ እየተደረገለት እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡

ከካርታ ጋር ተያይዞ በትምህርት ቤቱ ላይ ካርታ ያወጣ አካል እንደሌለ ለዝግጅት ክፍሉ አስረድተዋል። ይሁን እንጂ የዝግጅት ክፍሉ በትምህርት ቤቱ ካርታ እንደወጣበት እና ለዚህም ማስረጃዎች እንዳሉ በተገለጸላቸው ጊዜ ምንም እንኳን ፌዴራል ቤቶች ካርታ ቢያወጣበትም ሁለቱም የመንግሥት ተቋማት ስለሆኑ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ሊያሳድር እንደማይችል አስረድተዋል፡፡

ጉዳዩ ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ ፍርድ ቤቱ ለቤቶች ኮርፖሬሽን ቢፈርድ እንኳን ጉዳዩን በድርድር መፍታት እንደሚቻል የሚናገሩት ዶክተር ሙላቱ፤ ትምህርት ቤቱን የቤቶች ኮርፖሬሽን ይወሰድ ቢባል እንኳን ችግሩን ለመቅረፍ በርካታ አማራጮች መኖራቸውን አመላክተዋል፡፡

ከወረዳ 06 ቦታ ይፈለግና ገነት ትምህርት ቤትን በሌላ ቦታ እንገንባው፤ አማራጭ ቦታ ለፌዴራል ቤቶች እንስጣቸው ወዘተ የሚሉትን መሰል አማራጮች መኖራቸውን ተናግረው፤ አሁን ላይ ግን ጥያቄው እስኪነሳ መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 ያለው አንድ እና ብቸኛዋ የአጸደ ሕፃናት የገነት አጸደ ሕፃናት በመሆኑ በየዓመቱ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ገነት አጸደ ሕፃናት ትምህርት ቤት ለማስመዝገብ ሲጋፉ እና ሲጎርፉ ይታያል። በመሆኑም ይሄን ለወረዳው ብቸኛ ትምህርት ቤት ለሌላ ተቋም አሳልፎ መስጠት የአካባቢውን ማኅበረሰብ ለተጨማሪ ጉዳት እና እንግልት መዳረግ አይሆንም? ተብለው የተጠየቁት ኃላፊው «በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ገነት ትምህርት ቤት አይዘጋም፤ ለማንም አይሰጥም» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ትምህርት ቤቱ የተያዘው በሸማቾች ቢሆን እንዳይሸጠው ስጋት ሊሆን ይችላል፡፡ አሁን ግን የተያዘው በመንግሥት ተቋም በመሆኑ ሊዘጋ ይችላል ከሚል እሳቤ የራቀ እንዲሆን ያስችላል ብለዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ሸማች በሚስተዳድራቸው 28 በሚደርሱ ትምህርት ቤቶች ላይ ጥናት ማስጠናታቸውን ተናግረው፤ አፈጻጸማቸው ጥሩ ባለመሆኑ ትምህርት ቤቶችን ከሸማቾች ወደ መንግሥት ለማስቀየር ለከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ በማሳወቅ ውሳኔ እየጠበቁ እንደሚገኝ ተናግረዋል። «ይሁን እንጂ የገነት ትምህርት ቤት ጋር በተያያዘ ከወላጆች የቀረበው ስጋት "ፕሪ ማቹርድ" ነው» ሲሉ መልሰዋል፡፡

አያይዘውም የዝግጅት ክፍላችን ስጋት እንደሚረዱት በመናገር፤ «ገነት የትም አይሄድም፤ ገነት አይዘጋም» ሲሉ ገልጸው፤ ይሁን እንጂ ባለይዞታ ነኝ የሚለው አካል ገና ጥያቄውን ሳያነሳ ይሄንን ነገር ወደ ሚዲያ ማምጣቱ በሁለቱ ተቋማት በኩል የሚኖረውን ግንኙነት ሊያሻክር እንደሚችል ስጋታቸውን ተናግረዋል፡፡

ትምህርት ቢሮው ለትምህርት ቤቱ ወጪ በማውጣት የተሻለ ትምህርት እንዲሰጥ ለማስቻል የተለያዩ ተግባራትን እየከወነ ሲሆን በዚህም እስካሁን ባለይዞታ የሆነው የፌዴራል ቤቶች ጥያቄም ሆነ ተቃውሞ አሰምቶ እንደማያውቅ አመላክተዋል፡፡

ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ሊቀርብና አስረክቡ ሊባል ይቅርና በጥያቄ መልክ እንኳን ለትምህርት ቢሮ አለመድረሱን ተናግረው፤ ነገር ግን የሆነ ቡድን ፍላጎት እንደሚኖርበት ገልጸዋል፡፡ ምናልባት በትምህርት ቤቱ ዙሪያ የሚገኙ መጠጥ ቤቶች ከኪራይ ቤቶች ሰዎች ጋር በመሆን አንዳንድ ሙከራዎችን አድርገው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ብዙ ርቀት አልሄዱበትም። ምክንያቱም የሚያዋጣ አይደለም፡፡ ገነት የሚባል ሕጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ግን ይቀጥላል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

## የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ምላሽ

ወይዘሮ አጻዱ ረጋሳ በፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ናቸው።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

# «በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ገነት ...

ከገጽ 6 የዞረ

የዝግጅት ክፍሉ ስለጉዳዩ ምን ያውቃሉ ሲል ጠይቆ ዳይሬክተሯ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውናል፡፡

ይህ ትምህርት ቤት በአዋጅ 47/67 ከተወረሰበት ጊዜ ጀምሮ ቤቱ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ሲያስተዳድረው የቆየ ነው። በአዋጅ 47/67 የተወረሰ ቤት ስለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎች አሉ። ከማስረጃዎች መካከል እንደማሳያ አንድ ቤት ሲወረስ የሚሞላ ቅጽ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህ ቅጽ ከማን ተወረሰ ከሚለው በደንብ የሚገልጽ ነው፡፡

ቤቱ የተወረሰው ወይዘሮ ትዝታ ዳንኤል ከሚባሉ ግለሰብ ነው፡፡ ወይዘሮ ትዝታ ትምህርት ቤቱን ከአባታቸው ከአቶ ዳንኤል የወረሱት ነበር። ነገር ግን ቤቱን ያከራዩት ስለነበር በትርፍ ቤትነት መንግሥት በአዋጅ 47/67 ወረሰው፡፡ ትምህርት ቤቱ የመንግሥት ስለነበር በወቅቱ አጠራር ኪቤአድ (የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ) ይባል ለነበረው በአሁኑ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን እንዲሰጥ ሆነ፡፡

ከግለሰቧ ወደ መንግሥት የተወረሰበት 004 ቅጽ በእጃቸው መኖሩን የሚናገሩት ዳይሬክተሯ፣ ቅጽ 004 አንድ ግለሰብ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሚያከራየው ቤት ካለ የሚፈልገውን ቤት አስቀርቶ ቀሪውን ለመንግሥት የሚያስረክብበት ማማረጫ ቅጽ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ቅጽ 003 ደግሞ መውረሻ መሆኑን ይናገራሉ፡፡

ቅጽ 004 ማማረጫ ከሆነ ሌላኛው ወይዘሮ ትዝታ ቤት የት ይገኛል? ቁጥሩስ ስንት ነው? የሚል ጥያቄ የተነሳላቸው ዳይሬክተሯ፤ ወይዘሮ ትዝታ መርጠው ያስቀሩበት ቤት የት ክፍለ ከተማ እና ቁጥሩ ስንት እንደሆነ እንደማያውቁ ይናገራሉ። «ወይዘሮ ትዝታ ስለመረጡት ቤት ማስረጃ የሚገኘው ከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ነው» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡


ወይዘሮ ትዝታ ትርፍ ቤት የላቸውም ግን የወረሱትን ቤት ያከራዩ ነበር፡፡ ስለዚህ የሚከራየው ቤት ደግሞ ትምህርት ቤት ስለነበር ለአከራይዋ ምትክ ቤት ተሰጥቷቸው ይህ ቤት ተወርሷል፡፡ አንድ ሰው በስሙ የተመዘገበ ትርፍ ቤት ሳይኖረው ቤቱን ስለአከራየ ብቻ እንዴት ሊወረስ ይችላል? የሚል ጥያቄ የተነሳላቸው ዳይሬክተሯ፤ «አዋጁ ላይ በተገለጸው መሠረት ግለሰብ ቤት ማከራየት አይችልም፡፡ ስለሆነም ተወርሷል፡፡» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

በአዋጅ ከተወረሰ በኋላ ከትምህርት ቤቱ ጋር የነበራችሁ ግንኙነት ምን ይመስላል? ትምህርት ቤቱ ላይ የእናንተ ሚና ምን ነበር? ተብለው የተጠቁት ዳይሬክተሯ፤ ትምህርት ቤቱ ኪራይ ለመክፈል ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ ይህን ተከትሎ በ1973 ዓ.ም ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ደብዳቤ ተጽፎላቸው ነበር፡፡ የቤቱ ኪራይ ግምት በወር 255 ብር እንዲከፍሉ የሚል ነው። ይሁን እንጂ በዚያ ደብዳቤ መሠረት ኪራይ ሊከፍሉ አልቻሉም፡፡

ትምህርት ቤቱ ከ1973 ዓ.ም ጀምሮ የኪራይ ውል እንዲዋዋል የተጠየቀ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ሳይዋዋል እየኖረበት ነው፡፡ ትምህርት ቤቱ የመንግሥት ስለሆነ ኪራይ እንዲከፍሉ ለማስገደድ በኮርፖሬሽኑ ብዙም ተገፍቶ አልተሄደበትም። ለዚህም እንደ ምክንያቱም ያነሱት ተማሪዎችን የሚያስተምር እና ማኅበራዊ አገልግሎት እየሰጠ ያለን ተቋም ኪራይ አልከፈልክም ብሎ ተማሪ በትኑ ማለት ተገቢ አለመሆኑን ነው። ለተከራየው ቤት ኪራይ አልከፍልም ያለው ግለሰብ ቢሆን ኖሮ ከቤቱ እንዲወጣ ይገደድ እንደነበር አመላክተዋል።

«ሕግ እና መመሪያን እስካልተከተለ ድረስ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሆንስ ለምን



አይጠየቅም?» ተብለው የተጠየቁት ወይዘሮ አጻዱ፤ በቤቱ አንድ ሰው ብቻ አይደለም የሚኖረው፤ ትምህርት ቤት ነው ፣ ትውልድ ነው እየተገነባበት ያለው፡፡ ሕግ ሕግ ነው ብለን መንግሥት ያገኘው የነበረውን ኪራይ ስላላገኘ ብቻ ትምህርት ቤቱ አይበትንም፡፡ እስካሁን ድረስ የቤቶች ኮርፖሬሽን ነገሩን አለሳልሶ ለማለፍ የሞከረው በዚሁ ምክንያት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

እንደዳይሬክተሯ ገለጻ፤ የቤቶች ኮርፖሬሽን በ2011ዓ.ም የኪራይ ተመን ማሻሻያ ባደረገበት ወቅት ኪራይ እንዲከፍል ለትምህርት ቤቱ ደብዳቤ ጽፎ ቢጠይቅም ኪራይ ሊከፍሉ ፈቃደኛ አልነበሩም። ይህን ተከትሎ ኪራይ የማይከፍሉ ተቋማት እና ድርጅቶችን ዝርዝር አዘጋጅተው ለአራዳ ክፍለ ከተማ እና ለአዲስ አባባ ከተማ አስተዳደር በደብዳቤ አሳውቋል። ከአሳወቃቸው መካከል የገነት አጸደ ሕፃናት አንዱ መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ነገር ግን ሕግ እና መመሪያ ስለሚድግፋቸው ብቻ ትምህርት ቤቱ እንዲበተን አለማድረጋቸውን ይናገራሉ፡፡

ስለዚህ እስከዛሬ ድረስ ከትምህርት ቤቱ ጋር የአከራይ እና ተከራይ ውል የላችሁም? ተብለው የተጠየቁት ወይዘሮ አጸዱ፤ ከትምህርት ቤቱ ጋር የአከራይ እና ተከራይ ውል እንዳላቸው ገልጸዋል። በ2004 ዓ.ም ከትምህርት ቤቱ ጋር የአከራይ እና ተከራይ ውል መዋዋላቸውን ያስረዳሉ፡፡ ሰነድም አቅርበዋል። ለዝግጅት ክፍላችን የቀረበው ሰነድ የሚያመላክተው ግን የኪራይ ውሉ ከትምህርት ቤቱ ጋር ሳይሆን ከአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 11/12 ወከለዋል በተባሉ ከአቶ አበበ የኔታ ጋር መሆኑን ማየት ችሏል፡፡

ለወይዘሮ አጸዱ ከተነሳላቸው በርካታ ጥያቄዎች መካከል እንደ ተቋም ካርታ ባላወጣችሁበት ቤት የምትዋዋሉበት አሠራር እና መመሪያ አለ? የሚል ነበር። «ከዚህ ቀደም በርካታ ቤቶች ካርታቸው የጠፋባቸው እና ካርታ የሌላቸው ነበሩ፡፡ በመሆኑም ቤቶች ካርታ ሳይኖራቸው ሊከራዩ የሚችሉበት ሁኔታ ነበር፡፡ አሁን ግን የኮርፖሬሽኑ ቤቶች መቶ በመቶ ካርታ ያላቸው በመሆኑ ካርታ ሳይኖራቸው አይከራዩም» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ቤቶች ኮርፖሬሽን ውዝግብ በተነሰባት ቤት ካርታ ያወጣው ሐምሌ 2004 ዓ.ም ነው። ከአቶ አበበ የኔታ ጋር የኪራይ ውል የተዋዋሉት ደግሞ ካርታ ከማግኘታቸው ቀደም ብሎ መሆኑን የመልካም አስተዳደርና ሥነ ምግባር ዝግጅት ክፍል ካገኛቸው የሰነድ ማስረጃዎች አረጋግጧል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ቤቱ የራሱ ከሆነ እስከ 2004 ዓ.ም ድረስ ለምን ውል አልተዋዋለም? ተብለው የተጠየቁት ወይዘሮ አጻዱ «ትምህርት ቤቱ ንብረቱ የእሱ ከሆነ ለምን በፍርድ ቤት ሄዶ ንብረቱን አያስመልስም ?» ሲሉ ጥያቄን በጥያቄ መልሰዋል፡፡

በ2004 ዓ.ም የኪራይ ውል የተዋዋሉት አቶ አበበ የኔታ በክፍለ ከተማው የነበራቸውን የሥራ ኃላፊነታቸው በውል ሰነዱ ላይ ስላልተገለጸ የአቶ አበበን የሥራ ኃላፊነት እንደማያውቁ ይናገራሉ፡፡

ካርታ ሲወጣ የሲአይኤስ እና የጂአይኤስ ማስረጃዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ ቤቱ የቤቶች ኮርፖሬሽን ስለመሆኑ የሲአይ ኤስ ማስረጃ ክፍለ ከተማ ሊኖር እንደሚችል ገልጸው፤ ነገር ግን የሲአይኤስ ማስረጃው በተቋማቸው መኖር እና አለመኖሩን እንደማያውቁ ተናግረዋል፡፡

ከተለያዩ ቦታዎች የተገኙ ማስረጃዎች እንደሚያመላክቱት ከአዋጅ 47/67 በኋላ በተጠቀሰው ቤት ትምህርት ቤቱ የተለያዩ ግንባታዎችን አካሂዷል፡፡ ይህ ሲሆን እንናተ አልተቃወማችሁም። ወይስ ፈቅዳችሁ ነው ቤቶች የተገነቡት? ለምሳሌ በመስከረም ወር 1997 ዓ.ም በተጠቀሰው ቦታ ላይ በርካታ ቤቶች ተሠርተዋል። አሁንም ቤቶቹ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። እንደዚህ ዓይነት ግንባታዎች ሲካሄዱ ቤቶች ኮርፖሬሽን እንደባለቤት ምን ዓይነት እርምጃዎችን ወሰደ? ተብለው የተጠቁት ዳይሬክተሯ «ስለጉዳዩ መረጃ የለኝም፡፡ እንደዚህ ነው ብዬ መግለጽ አልችልም፡፡» ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ቤቶች ሲሠሩ የግንባታ ፈቃድ ከክፍለ ከተማ ወይም ከወረዳ ተሰጥቷቸው ነው የሚገነቡት፡፡ የሲአይ ኤስ መረጃ የእናንተ መሆኑን የሚያሳይ ከሆነ እንዴት በሰው ይዞታ የግንባታ ፈቃድ ሊሰጥ ቻለ? ተብለው በዝግጅት ክፍሉ የተጠቁት ዳይሬክተሯ «ይህንን ክፍለ ከተማ ነው መጠየቅ ያለባችሁ፡፡ እኛ በይዞታችን ላይ የተጨማሪ ግንባታ አንፈቅድም። በቦታው ላይ ተጨማሪ ግንባታ ተካሂዶ ከሆነ የሚጠየቀው ከተማ አስተዳደሩ ነው፡፡ የእኛ ተቋም አዲስ የግንባታ የሚፈቅድ ሳይሆን የነበረን ማደስ በተመለከተ ነው ሥልጣን ያለው ፡፡» ሲሉ መልሰዋል፡፡

በወቅቱ ትምህርት ቤቱ ሲወረስ የቤቶች ብዛት ስንት እንደነበር እንደማያውቁ የሚገልጹት ዳይሬክተሯ፤ የተወረሱ ቤቶችን ቁጥር ከተወረሰበት ቅጽ ላይ ማግኘት እንደሚቻል አመላከተዋል፡፡

ትምህርት ቤቱ ካርታ ለማሠራት እና መብት ለማስፈጠር በሚንቀሳቀስበት ወቅት ከ1964 ዓ.ም ጀምሮ በስሙ የተመዘገበ የመብራት መሠረተ ልማት፣ ሌሎች የግብር ክፍያዎች መኖራቸውን ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እናንተስ በቤቱ የተመዘገበ የመብራት እና የውሃ መሠረተ ልማት ተጠቃሚነት ማስረጃዎች አሏችሁ? የአፈር ግብርስ ትከፍሉ ነበር? ተብለው አስተያየታቸውን የተጠየቁት ወይዘሮ አጻዱ፤ ትምህርት ቤቱ የውሃ እና የመብራት አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በአዋጅ 47/67 አልተወረሰም ማለት ግን አይደለም። የውሃ እና የመብራት አገልግሎት የቤት ባለቤትነት መብት ሊያሰጥ እንደማይችልም ጠቁመዋል፡፡

ቤቶች ኮርፖሬሽን በ2004 ዓ.ም ካርታ ሲያሠራ በሰነድ አልባ መብት ተፈጥሮለት አይደለም በአዋጅ 47/67 በውርስ ስላገኘው ሰነድ ስላለው እንጂ ያሉት ዳይሬክተሯ፤ የባለቤትነት ሰነድ ግን ለዝግጅት ክፍላችን ማቅረብ አልቻሉም፡፡ ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ጥልቅ መረጃ እንደሌላቸው እና ከካርታ ጋር በተገናኘ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የቤቶች ኮርፖሬሽን ክፍሎች ስላሉ እነሱን ማነጋገር ይቻላል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

የአራዳ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ወረዳ 06ን ትምህርት ቤቱን እንደሚያስተዳድረው እና እንደማያስተዳድረው ተጠይቆ ነበር፡፡ ለዚህ ምላሽ የሰጠው ወረዳ 06 «የቤት ቁጥር 1371 የገነት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቦታውን ወረዳው የማያስተዳድረው የመንግሥት ይዞታ ነው፡፡» ሲል ገልጸዋል፡፡ በዚህ ላይ የቤቶች ኮርፖሬሽን ምላሽ ምንድን ነው? ተብለው የተጠየቁት ዳሬክተሯ፤ በወረዳ 06 ከተሰጠው ምላሽ እንደተመላከተው የቤት ቁጥር 1371 የገነት ትምህርት ቤት ነው፤ ነገር ግን ወረዳው የማያስተዳድረው የመንግሥት ይዞታ ማለቱ ቤቱ የቤቶች ኮርፖሬሽን መሆኑን የሚጠቁም መሆኑን ዳይሬክተሯ ይናገራሉ፡፡ ይህን ተከትሎ የቤት ቁጥር 1371 የገነት ትምህርት ቤት ነው፤ መሬቱን መንግሥት እንጂ ወረዳው አያስተዳድረውም ማለት እንዴት ሆኖ ነው ቤቱ ኮርፖሬሽኑ ነው የሚል ትርጉም የሚሰጠው? ተብለው የተጠየቁት ዳይሬክተሯ «እኔ የምረዳው እንደዚህ ነው!» ብለዋል፡፡

የገነት ትምህርት ቤት የሕዝብ ትምህርት ቤት የነበረ ነው፡፡ የሕዝብ ማለት ደግሞ የመንግሥት ማለት ነው በሚል የተከራከሩ ሲሆን፤ የሕዝብ ትምህርት ቤት ማለት የመንግሥት ማለት አይደለም በሚል ዝግጅት ክፍሉ ገለጻ ቢያደርግም ሊረዱት አልቻሉም፡፡ በዚህም ከ2004 ዓ.ም በፊት የሕዝብ ትምህርት ቤት የሚባሉ እንደነበሩ እና እነዚህም ትምህርት ቤቶች በመንግሥት የተቀረጸውን ሥርዓተ ትምህርት ያስተምሩ እንጂ ባለቤትነታቸው የሕዝብ እንደነበሩ መረጃው እንደሌላቸው ተረድቷል፡፡

ኮርፖሬሽኑ የሚያስተዳድራቸው እንደ ገነት ዓይነት ትምህርት ቤቶች ይኖራሉ ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ይሁን እንጂ በቁጥር ለመግለጽ እንደሚቸገሩ አመላክተዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ ንብረቶች ላይ ሌላ ወገን ግብር ሊከፍልበት የሚያስችል አሠራር አለወይ? የሚል ጥያቄ የተነሳላቸው ዳይሬክተሯ፤ «እኛ ምን አገባን እና ካርታ አለን፡፡ እኛ ካርታ ካለን በቂያችን ነው። ሌላ አካል የአፈር ግብር ሆነ የመሬት ግብር ቢገብር አይመለከተንም» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የምናወራው ከሕግ እና ከመመሪያ አኳያ ነው። መመሪያ አለወይ? ተብለው ለተነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ስለአፈር ግብር የሚገልጽ መመሪያ እንደሌለ ተናግረዋል፡፡

ዝጅግት ክፍላችን ውዝግብ በተነሳበት ቦታ ገነት ትምህርት ቤት ግንባታ ሲያከናውን ስለምን ዝም አላችሁ? ተብለው የተጠየቁት ዳይሬክተሯ፤ ስለግንባታ እንደማይመለከታቸው ተናግረዋል፡፡

### የጋዜጠኞች ትዝብት

ተወረሰ የተባለው ቤት ስፋት ሁለት ሺ 380 ካሬ ሜትር ሲሆን አሁን ካርታ የተሠራበት ግን አንድ ሺ 780 ነጥብ 81 ካሬ ሜትር ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር የተወረሰው ቤት ከመሐል ከተማ ወረዳ 09 ሲሆን ውዝግብ የተነሳበት ቤት መገኛ ግን ከፍተኛ 13 ወረዳ 03 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በመጨረሻም፡- የሰነድ ማስረጃዎችን እና ቀሪ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ምላሽ በሚቀጥለው የምርመራ ዘገባ ክፍል ይዘን የምንቀርብ ይሆናል፤ እስከዚያው ቸር እንሰንብት፡፡

# የባህር በር ስምምነቱ በዓለም መድረክ የመደራደርና የኃይል ሚዛንን የማስጠበቅ አቅምን ያሳድጋል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር የተፈራረመችው የባህር በር ስምምነቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመደራደርና የኃይል ሚዛንን ለማስጠበቅ አቅም እንደሚያሳድግላት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የኮሙኒኬሽንና የፐብሊክ ዲፕሎማሲ መምህርና ተመራማሪ ደመላሽ መንግስቱ (ዶ/ር) አስታወቁ።

ደመላሽ መንግስቱ (ዶ/ር) በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የባህር በር ባለቤት ለመሆን ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር የተፈራረመችው ስምምነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የኃይል ሚዛንን ለማስጠበቅና የመደራደር አቅምን ለማሳደግ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

የባህር በር ባቤት መሆን የኃይል ሚዛንን በማስጠበቅ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከማምጣት ባሻገር የሀገሪቱን ሁለንተናዊ አቅም ያሳድጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤት ለመሆን መክፈል ያለባትን የዲፕሎማሲ ዋጋ መክፈል አለባት የሚሉት ተመራማሪው፤ ለዚህ ደግሞ ከሶማሌላንድ ጋር የተጀመረው ግንኙነት መጠናከርና ወደ ተጨባጭ ደረጃ መሻገር አለበት ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፍላጎት ከጎረቤት ሀገራት ጋር በጋራ መልማትና መበልጸግ መሆኑን የተለያዩ ሚዲያዎችን ተጠቅሞ ማስረዳት አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የባህር በር አልባ እንድትሆን የምእራባውያን አስተሳሰብ አራማጆች እንዳሉ የጠቀሱት ተመራማሪው፤ የዚህ መነሻ ኢትዮጵያ ያለችበት የጂኦ ፖለቲካ አቀማመጥ መሆኑን አመልክተዋል።

ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ የባህር በር ብትቆጣጠር በቀጣናውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሊኖር የሚችል የኃይል ሚዛን ወደ ሀገሪቱ ሊያጋድል እንደሚችል ጠቁመዋል።

ይህ ለምዕራባውያን የሚዋጥ ጉዳይ ባለመሆኑ ኢትዮጵያን የባህር በር አልባ እንደትሆን ሲጥሩ ቆይተዋል። ነገር ግን የባህር በር ባለቤት ለመሆን የሚደረገው ጥረት



**ደመላሽ መንግስቱ (ዶ/ር)**

መጠናከርና እንዳለበት አስረድተዋል።

እንደ ደመላሽ/ዶ/ር/ ገለጻ፤ የባህር በር ስምምነቱ በአሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ እድገት ትልቅ ሥራ የሚሰሩ ባለሙያዎች እንዳሉ ማሳያ ነው።

ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ውስጥ የተሰሩት የዲፕሎማሲ ስራዎች ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ድል ያስመዘገብንባቸው ናቸው። በይፋ ብሪክስን መቀላቀልን ጨምሮ ከሰሞኑን ኢትዮጵያ የወደብ ባለቤት እንድትሆን የሚደረገው እንቅስቃሴ በራሱ ትልቅ የዲፕሎማሲ ድል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል ብለዋል።

ስለ ባህር በር ባለቤትነት ሲወራ ቀጣናው እንደሚበጠበጥ የሚያስፈራሩ አካላት እንዳሉ የጠቀሱት ደመላሽ/ዶ/ር/ ፤ ይህ ሃሳብ የተሳሳተ መሆኑን ለማስረዳት የዲፕሎማቶች የማሳመን አቅም ወሳኝነት እንዳለው አመላክተዋል። ኢትዮጵያ ያለምንንም ግጭት የባህር በር እንዲኖራት ማስረዳት ተገቢ መሆኑን ጠቁመዋል።

# በመዲናዋ የሚገኙ ከ30 ሺህ በላይ ግንባታዎች ላይ የጥራትና ቁጥጥር ሥራ እየተሠራ ነው

## - ከ45ሺህ በላይ ማስታወቂያዎች ተነስተዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በሂደት ላይ የሚገኙ ከ30ሺህ በላይ ግንባታዎች ላይ የጥራት ደረጃና የደህንነት ቁጥጥር እየተከናወነ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን አስታወቀ። በየመንገዱ የተሰቀሉ ከ45ሺህ በላይ ሕገወጥ ማስታወቂያዎች ተነስተው ወደዲጂታል ሥርዓት እንዲገቡ አቅጣጫ ተቀምጧል።

የባለስልጣኑ የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ዳይሬክተር ከማል ጀማል (ኢ/ር) ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ በአጠቃላይ ከወረዳ ጀምሮ እስከ ማዕከል በተለያዩ ግለሰቦችና ተቋማት አማካኝነት ከ30ሺህ በላይ ግንባታዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

ግንባታዎቹ ጥራትና ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ በተቋም ደረጃ ልዩ እቅድ ተዘጋጅቶ ክትትል እየተደረገ ነው ያሉት ኢንጂነር ከማል፤ የግንባታ ጥራትና ደህንነት ጥንቃቄዎችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ የፍቃድ አሰጣጥና የክትትል ሥርዓቱ በወረዳ፣ በክፍለ ከተማና በማዕከል ደረጃ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

የህንጻ ግንባታዎች በተዘጋጀላቸው ዲዛይንና ቦታ ላይ መከናወናቸውን የሚከታተል ክፍል መኖሩንና፤ ማንኛውም አልሚ የግንባታ ደህንነት መሟላቱን አረጋግጦ ህንጻውን ማጠናቀቅ እንዳለበት አመላክተዋል።

ከተማዋን ስማርት ሲቲ ለማድረግ እየተሠራ ባለው ሥራ የማስታወቂያ፣ የመሰረተ ልማትና የሌሎችንም ግንባታዎች ለመቆጣጠር በልዩ ሁኔታ ከጥቅምት ወር ጀምሮ እቅድ ወጥቶ ከማዕከል እስከ ወረዳ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

በዋና ዋና መስመሮች የከተማ ገጽታን የሚያበላሹ የአጥር ግንባታዎች እንዲስተካከሉ፣ የህንጻ ሽፋኖች ደረጃቸውን እንዲጠብቁና በግንባታ ወቅት የሰራተኞች ደህንነት እንዲጠበቅ ክትትል እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

ኢንጂነር ከማል እንዳመለከቱት፤ የህንጻ ሽፋን፣ የአጥር ደረጃ፣ የግንባታ ግብዓትና ተረፈ ምርት በመንገድ ላይ የሚያስቀምጡና በህንጻ ደህንነት ላይ ችግር የተገኘባቸው አልሚዎች፣ የግንባታ አማካሪዎችና ኮንትራክተሮች ላይ የማስተካከያ ርምጃ እየተወሰደ ይገኛል።

የግንባታ ግብዓቶች በእግረኛ መንገዶች ላይ በሚያስቀምጡ በመሰረተ ልማቶች ላይ ጉዳት ያደረሱ ሦስት ሺህ የሚጠጉ አካላት ላይ ርምጃ በመውሰድ ግብዓቶቹን የማንሳት ሥራ ተከናውኗል ሲሉ አስረድተዋል።

በተጨማሪ የከተማዋን ውበት በማበላሸት በየመንገዱ የተሰቀሉ ከ45ሺህ በላይ ማስታወቂያዎች እንዲነሱና በዋና ዋና መንገዶች ላይ በዲጂታል ማስታወቂያዎች እንዲተኩ መደረጉን ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

በመንገድ ዳር በተለያዩ ተለጣፊና ተንጠልጣይ መንገዶች የሚሰቀሉ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ማስታወቂያዎች ህጋዊነታቸው ያልተረጋገጡና የመንገድ ደህንነት ህግን ያላከበሩ በመሆናቸው በቀጣይም የማስተካከሉ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በከተማዋ ዋና ዋና አካባቢዎች የተሰቀሉ ዲጂታል የማስታወቂያ ቦርዶች ዘመናዊነትን የተላበሱና በውበትም የተመረጡ በመሆናቸው ማንኛውም ማስታወቂያ ያለው አካል ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመነጋገር ወደዘመናዊ ሥርዓቱ መግባት እንደሚችል አስረድተዋል።

# ኢትዮ ቴሌኮም

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

መድረሱን ጠቁመው፤ አገልግሎቱ ከተጀመረም እስካሁን አንድ ነጥብ ሰባት ትሪሊዮን ብር ማንቀሳቀስ ችሏል ብለዋል። እነዚህ ውጤቶች ሊመዘገቡ የቻሉትም ተቋሙ አዳዲስ ምርትና አገልግሎቶችን ለገበያ በማቅረቡና በነባሮቹም ላይ ማሻሻያ በመደረጉ መሆኑንም ገልጸዋል።

በገቢ ረገድም በግማሽ ዓመት ውስጥ 42 ነጥብ 86 ቢሊዮን ብር ገቢ ያገኘ መሆኑን አመልክተው፤ ከዚህ ውስጥ 11 ቢሊዮን ብሩ የተጣራ ትርፍ ሆኖ ተመዝግቧል። ወጪን በአግባቡ ከመጠቀም ረገድ ስትራቴጂ ተነድፎ በተሠሩ ስራዎችም ከሁለት ቢሊዮን ብር በላይ የወጪ ቁጠባ በማድረግ ከእቅድ በላይ ማሳካት ተችሏል ነው ያሉት።

የሞባይል ኔት ወርክ ሽፋንና አቅም ለማሳደግ ባለፉት ስድስት ወራት በተከናወኑ ተግባራት በ3ጂ በ4ጂና በ5ጂ 232 የሞባይል ጣቢያዎች የተገነቡ መሆኑን አውስተው፤ 463 ጣቢያዎች ደግሞ የ4ጂ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ መቻሉን ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሪት ፍሬህይወት ገለጻ፤ እነዚህ ሥራዎችም ከአንድ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የሞባይል ተገልጋዮችን ማስተናገድ የሚያስችል ሲሆን፤ አጠቃላይ አቅሙንም 81 ሚሊዮን የሚያደርስ ይሆናል። በአጠቃላይም 340 ከተሞች የ4ጂ አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነዋል።

ኢትዮ ቴሌ ኮም የሶስት ዓመት ሊድ የእድገት ስትራቴጂ ቀርጾ መንቀሳቀስ ከጀመረ ዓመት ከስድስት ወር ሆኖታል ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ የስድስት ወሩ አፈጻጸም በስትራቴጂው የተቀመጠውን በሀገሪቱ እየተገነባ ያለውን ዲጂታል ኢኮኖሚ ውጤታማ መሆንን ታሳቢ ያደረገ እንደሆነ ገልጸዋል።

# የኢትዮጵያ አየር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጉብኝቱ በአዲስ አበባ የተሰሩና በመሰራት ላይ ያሉትን የቱሪስት መስህቦች ለማስተዋወቅ እንደሚረዳ ገልጸው፤ በጉብኝቱ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ስለ ሀገራቸው የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

ለሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን ከጉዞ ትኬትና ከስካይላይት ሆቴል አገልግሎት ክፍያ ከ15 እስከ 20 በመቶ ቅናሽ ተደርጓል ያሉት ኃላፊው፤ የዋጋ ቅናሹን ተጠቅመው በርካታ ቁጥር ያላቸው እንግዶች በአየር መንገዱ በረራ እየመጡ ነው ብለዋል።

ሀገራዊ ጥሪውን ተቀብለው በርካታ ቁጥር ያላቸው የሁለተኛው ትውልድ የዳያስፖራ አባላት በመምጣት ላይ መሆናቸውን አመላክተው፤ በጥሪው መሰረት በቀጣይ ምዕራፍ ለመምጣት የተዘጋጁና የተመዘገቡ መኖራቸውን ጠቁመዋል።

አየር መንገዱ መንገደኞችን የተለያዩ ዕቃዎችን በማጓጓዝ የሆቴል አገልግሎቶችን እንደሚሰጥ የገለጹት አቶ ለማ፤ ወደ ሀገር ቤት የሚመጡ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያውያን አባላትና ቤተሰቦቻቸው የዋጋ ቅናሹ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

በተጨማሪም አየር መንገዱ በውጭ ሀገር ለሚኖሩ የሁለተኛው ትውልድ ኢትዮጵያዊያን አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያደርግ መሆኑን ጠቁመው፤ ወደ ሀገራቸው እንዲመጡና እንዲጎበኙም ጥሪ አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ባቀረቡት ጥሪ መሰረት በርካታ ዜጎች እየመጡ መሆኑ ይታወቃል።

# መንግሥት ግጭት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን በኢትዮጵያ ለሚገኙ የዓለም አቀፍ ተቋማትና የተለያዩ ሀገራት ወታደራዊ አታሼዎች ስለወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ ሰሞኑን ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት፤ የፌዴራል መንግሥት ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ሰላም ለማስፈን በቁርጠኝነት እየሠራ ነው።

በአማራ ክልል የነበረው የጸጥታ ችግርም በመከላከያና በክልሉ የፀጥታ ኃይሎች በቁጥጥር ስር መዋሉን ጠቁመው፤ መንግሥት ማንኛውንም ችግር በውይይትና በድርድር እንጂ በአፈ-ሙዝ የመፍታት አላማ የሌለው መሆኑን አሳውቀዋል።

በክልሉ ለሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪ ማድረጉን ተናግረው፤ በአሁን ወቅትም በክልሉ ሰላማዊ እንቅስቃሴ መኖሩን አብራርተዋል።

በኦሮሚያ ክልልም ሰላምን ለማስፈን በተመሳሳይ መልኩ የተለያዩ የጸጥታ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አንስተው፤ በሸኔ ላይ እየተወሰደ ባለው ርምጃ ውጤት እየተገኘ መሆኑን አመላክተዋል።

ከቡድኑ ጋር ስምምነት ለመፍጠር በተደረገው ጥረት ምንም አይነት የፖለቲካ አጀንዳ የሌላቸው ጉዳዮች መነሳታቸውን አምባሳደር ሬድዋን ገልጸው፤ እንዲህ አይነት አደረጃጀቶች ሕዝቡን ከማሸበርና የራሳቸውን ጥቅም ከማስጠበቅ ውጪ ዓላማ የሌላቸው ናቸው ሲሉ ተናግረዋል።

የትጥቅ እንቅስቃሴን አማራጭ የሚያደርግ አካልም በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በኩል ለመነጋገር መዘጋጀት እንዳለበት አንስተዋል።

በሌላ በኩል በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል በፕሪቶሪያ በተደረገው የሰላም ስምምነት ማግስት ለክልሉ ዓመታዊ በጀት ከመመደብ ጀምሮ በህግ ማስከበር ወቅት ሙሉ ለሙሉና በከፊል ጉዳት የደረሰባቸውን መሰረተ ልማቶችን በመጠገን አገልግሎት እንዲሰጡ መደረጉን አስታውሰዋል።

የግብርና፣ የጤናና የትምህርት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ከአጋር አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረጉ ሲሆን ለዜጎች የሚደረገው የሰብዓዊ እርዳታም ተጠናክሮ ቀጥሏል ብለዋል።

አምባሳደር ሬድዋን እንዳመለከቱት፤ የወደሙ የጤናና የትምህርት ተቋማትን በመጠገን በግጭቱ ተሳታፊ የነበሩ መምህራን፣ የጤና ባለሙያዎችና ሌሎችንም ወደሥራቸው እንዲመለሱ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

የፌዴራል መንግሥት የሕክምና መሳሪያዎችን፣ መድኃኒትና የተለያዩ ቁሶችን ድጋፍ እያደረገ እንደሆነም ጠቁመው፤ በክልሉ የሚገኙ ሥራ አጥ ዜጎችን በግብርናው ዘርፍ መሳተፍ ለሚፈልጉ የማሽነሪና የማዳበሪያ እገዛ ማድረጉን አስታውሰዋል፤ በግላቸው ቢዝነስ መጀመር ለሚፈልጉት የስልጠናና ገንዘብ ድጋፍ መደረጉንም አስታውቀዋል።

ባንክ፣ ቴሌኮምና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች መስጫ ተቋማትም ሥራ እንዲጀምሩ የተደረገ ሲሆን፤ እንዲሁም ድልድዮችና መንገዶችም ጥገና እንደተደረገላቸው አምባሳደሩ አንስተዋል።

በግጭቱ ወቅት ወንጀል የፈፀሙ አካላት ላይ አስፈላጊውን ማስረጃ በማጠናከር ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት እየተሠራ መሆኑንም አስረድተዋል።

ክልሉንና ተጎጂዎችን መልሶ ለማቋቋም የተለያዩ ዓለም አቀፍ አጋር አካላት ድጋፍ እያደረጉ መሆኑንም ጠቁመው፤ ስምምነቱ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን መንግሥት በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑንም አምባሳደር ሬድዋን አብራርተዋል።

በአማራና በትግራይ ክልሎች መካከል ያለው የድንበር አለመግባባት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በመከተል በህዝብ ውሳኔ ምላሽ እንደሚያገኝ አመላክተዋል።

# የሆርቲካልቸር ዘርፍ የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ለማሳደግ



ወርቅነሽ ደምሰው

ኢትዮጵያ በሆርቲካልቸር ልማት ከፍተኛ እምቅ ሀብት ካላቸው በቀዳሚነት ከሚጠሩት ሀገሮች ተርታ ትጠቀሳለች። ያላት ሰፊ መሬትና የአየር ንብረት ለሆርቲካልቸር ልማት ተስማሚ እንደሆነም ይነገራል።

ይህን እምቅ ሀብት በመጠቀም አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ሥራሥር ሰብሎች፣ እጸ ጣዕም፣ ቅመማቅመም፣ ቡና፣ ሻይና ሌሎችንም የሆርቲካልቸር ሰብሎችን አልምቶ ለውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪን ከማስገኘት አኳያ ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። ሀገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከምታገኝባቸው የግብርና ምርቶች አንዱ ይኸው የሆርቲካልቸር ልማት መሆኑ ይታወቃል።

የግብርና ሚኒስቴር የሆርቲካልቸር ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብዳላ ነጋሽ ፤ በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት በእንሰትና ሥራሥር ሰብል ልማት 32ሺ. 580 ቶን ለማምረት ታቅዶ፤ ከ33ሺ.681 ቶን በላይ ማምረት ተችሏል። በአበባ ልማት ከ69 ሺ. 341 ቶን በላይ ለማምረት ታቅዶ፤ ከ51ሺ.683 ቶን በላይ ተመርቷል። በፍራፍሬ ልማት 26ሺ.197 ቶን ለማምረት ታቅዶ፤ ከ25ሺ. 273ቶን በላይ ተመርቷል። በአትክልትና እጸ ጣዕም ልማት 115ሺ. ቶን ለማምረት ታቅዶ 91ሺ.596 ቶን ማምረት ተችሏል።

ለውጭ ገበያ ከተላኩት የሆርቲካልቸር ሰብሎች ውስጥ ከ29ሺ. 288 ቶን በላይ የእንሰትና ሥራሥር ሰብል፣ ከ46ሺ. 984 ቶን በላይ የአበባ ምርት፣ ከ21ሺ.276ቶን በላይ ፍራፍሬ፣ ከአትክልትና እጸ ጣዕም ከ74ሺ. 336 ቶን በላይ ምርቶችን ለውጭ ገበያ እንዲቀርብ ተደርጓል። ከእነዚህ የሆርቲካልቸር ሰብሎች የወጪ ንግድም በአጠቃላይ 298 ሚሊዮን 794ሺ. 887ነጥብ 45 የአሜሪካ ዶላር ገቢ ማግኘት ተችሏል።

በሆርቲካልቸር ሰብሎች ከምርት አንጻር ሲታይ በአንዳንድ ሰብሎች በ2015 በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ወደ ውጭ የተላከው ምርት መቶና ከመቶ በላይ መላክ የተቻለበት ነው ያሉት አቶ አብደላ፤ ከተላከው ምርት የተገኘው ገቢ ግን ዝቅ ያለ መሆኑን አመልክተዋል። ከተላከ ምርት አኳያም ቅናሽ ያሳየ ምርት እንዳለ ጠቅሰው፣ ለውጭ ገበያ የተላከው የእንሰትና ሥራሥር ሰብል እና የአበባ ምርት መጠን መቀነስ ማሳየቱን ተናግረዋል። ገቢውም የዚያኑ ያህል የቀነሰበት ሁኔታ እንዳለ ነው ያስታወቁት።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የበጀት ዓመቱ የመጀመሪያ ስድስት ወራት ግምገማ መረዳት እንደተቻለው፤ የሆርቲካልቸር ሰብሎችን ለውጭ ገበያ ከመላክ አኳያ ከታቀደው አንጻር መቶና ከመቶ በላይ አፈጻጸም ታይቷል፤ ከተላከው ምርት የተገኘው ገቢ ግን ቀንሷል። ወደ ውጭ የተላከው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርት ካለፈው 2015 በጀት አመት ተመሳሳይ ወቅት አንጻር ሲታይ ጭማሪ አሳይቷል።

የተላከው ምርት ከጨመረ የሚያስገኘውም የውጭ ምንዛሬ ገቢ መጠን መጨመር እንዳለበት ይታወቃል ያሉት አቶ አብደላ፣ ገቢው ግን መቀነሱን ነው ያስታወቁት። ይህ የሆነበት ምክንያት መጠናት እንዳለበት አስታውቀው፣ ከንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ጋር ጥናቶችን በማካሄድ መፍትሔዎች ላይ አቅጣጫ ማስቀመጥ ያስፈልጋል ብለዋል።

የሆርቲካልቸር ሰብሎች በተለያየ መንገድ ለውጭ ገበያ እንደሚላኩ መሪ ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰው፣ ምርቶቹ በየብስ እና በአየር ትራንስፖርት እንደሚላኩ ተናግረዋል። በየብስ ትራንስፖርት ወደሚላክባቸው አካባቢዎች በተለያዩ ችግሮች ሳቢያ ከሚመረተው ምርት አንጻር የሚፈለገውን ያህል የምርት የማይላክበት ሁኔታ እንደሚያጋጥም ተናግረዋል። በዚህ የተነሳ የሚፈጠሩ ክፍተቶች እንደ ችግር እንደሚነሱ ጠቅሰዋል።

ሌላኛው ምክንያት ደግሞ አብዛኛዎቹ አርሻዎች ዘር ከውጭ እንደሚያስገቡ ጠቅሰው፣ በዚህም ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ሊመረት እንደሚችል ይናገራሉ። ምርቱ በሚፈለገው ጥራት ካልተመረተ እና በሚፈለገው መጠን መላክ ካልተቻለ የዚያኑ ያህል ለውጭ ገበያ የሚላከው መጠን ሊቀንስ እንደሚችልም ነው አቶ አብዳላ ያስረዱት።

አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ምርቱ በበቂ ሁኔታ እንደተመረተ የሚያሳይ ሁኔታ እንዳለም ተናግረዋል። በአንጻሩ በአበባ ልማቱ አዳዲስ ዝርያዎችን የመተካት ሥራ እየተሠራ ያለበት ሁኔታ እንዳለም ይጠቁማሉ። ይህ ሁኔታ የመጀመሪያው ስድስት ወር አፈጻጸምን ሊቀንስ እንደሚችል ተናግረው፣ በቀጣዮቹ ስድስት ወራት ውስጥ ደግሞ ሊጨምር የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን አመላክተዋል።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ምርቶቹ የሚላኩባቸው በርካታ የውጭ ሀገራት የገበያ መዳረሻዎች እንዳሉም ጠቅሰው፣ የአበባ ምርት በአብዛኛው ለአውሮፓ ገበያ እንደሚቀርብ አስታውቀዋል። ከእነዚህ ሀገሮች ቀዳሚዋ የገበያ መዳረሻ ኔውዘርላንድ መሆኗን ጠቅሰዋል።

የእንሰትና የሥራሥር ሰብል ምርቶችን እንዲሁ ወደ ተለያዩ ሀገራት እንደሚላኩ ተናግረው፣ ምርቶቹ በተለይ ከምሥራቅ አፍሪካ ጀምሮ እስከ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ገበያ እንደሚቀርቡም አመልክተዋል። አብዛኛዎቹ በኢንቨስትመንት ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች እና ከአርሶ አደሩ ተረክበው የሚልኩ ላኪዎች ደግሞ ወደ አውሮፓና ሌሎች ሀገራት ይልካሉ ብለዋል።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው በሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት በርካታ አልሚዎች መሰማራታቸውን ጠቅሰዋል። ከእነዚህ ውስጥ ከ68 በላይ ባለሀብቶች በአበባ ልማት መሰማራታቸውን አመልክተው፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የተሰማሩ ባለሀብቶች ውስን መሆናቸውን ጠቅሰዋል። የሆርቲካልቸር ምርቱን ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑም ጠቅሰው፣ ሌሎች ምርቱን አሰባስበው ወደ ውጭ የሚልኩ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት እንዳሉም ይጠቁማሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሆርቲካልቸር ምርቶች በተለያየ መንገድ ለውጭ ገበያ ከሚልኩት ውስጥ አምርተው የሚልኩ እንዳሉ ሁሉ ለአምራቹ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ምርቱን ተቀብለው ለውጭ ገበያ የሚልኩ እንዳሉም አስታውቀው፣ ምርቱን ብቻ በማሰባሰብ የሚልኩ እንዳሉም ጠቅሰዋል።

ዘርፉ ለምን ያህል ሰዎች የሥራ ዕድል እንደፈጠረ እስከ አሁን በጥናት የተለየ መረጃ እንደሌለ ጠቅሰው፣ ‹‹የሆርቲካልቸር ሰብል ልማት ዘርፍ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር ይታመናል›› ሲሉም አቶ አብደላ አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በአብዛኛዎቹ የአበባ እርሻዎች፣ አትክልትና እጸ ጣዕም በብዛት በሚያመርትባቸው አካባቢዎች እስከ 200 /ሁለት መቶ/ ሺ ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ስለመፈጠሩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ከ10 እስከ 15ሺ. ሄክታር በማይበልጥ መሬት ላይ የሚካሄድ የሆርቲካልቸር ልማት የፈጠረው የሥራ ዕድል ነው። እስካሁን ያለው መረጃ በአግባቡ ያልተያዘ ቢሆንም፣ በእያንዳንዱ የሆርቲካልቸው ልማት በአማካኝ በሄክታር ከ18 እስከ 30 ለሚደርሱ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይገመታል። ይህን ደግሞ ከለማው ሄክታር አኳያ ሲታይ ልማቱ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል እየፈጠረ ስለመሆኑ መረዳት ይቻላል።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው የዘርፉ ዋንኛ ተግዳሮት ያሉትንም ጠቅሰዋል። ለኢንቨስትመንቱ በሚያስፈልጉት የቴክኖሎጂ አቅርቦቶች ላይ ክፍተቶች እንዳሉ አስታውቀው፣ ለዘርፉ ከሚያስፈልገው ቴክኖሎጂ አብዛኛው ከውጭ እንዲገባ ተደርጎ እንደሚሠራ አንስተዋል። ከኬሚካል ማዳበሪያ ጋር ተያይዞ ያለውን ተግዳሮት ለመቀነስ በሀገር ውስጥ ባዮሎጂካል የሆኑ ምርቶችን በማምረት ለመጠቀም የሚያስችሉ ጥሩ ሥራዎች መጀመራቸውንም ይገልጻሉ።

ለዘርፉ የሚያስፈልጉ ኬሚካሎችን ለማስገባት እና የተለያዩ ለኢንቨስትመንቱ ወሳኝ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ ከውጭ ምንዛሪ ጀምሮ ችግሮች ሲያጋጥሙ እንደነበር አስታውሰው፣ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በመንግሥት በኩል ጥረቶች መደረጋቸውንም አስታውቀዋል። በዚህም ችግሮቹን ሊቀርፍ የሚችል የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን ገልጸዋል።

ሌላኛው ተግዳሮት አምራች የሰው ኃይል ከማፍራት ጋር ተያይዞ የሚነሳው መሆኑንም መሪ ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ዘርፉ በሚጠይቀው ልክ ክህሎትና እውቀት ያለው የሰው ኃይል አብቅቶ ማቅረብ ላይ እጥረት ይታይ ነበር። ይህንንም ተግዳሮት ለመፍታት በግል በተከፈተ አንድ የቴክኒክና ሙያ የሆርቲካልቸር ኮሌጅ በኩል ጥረቶች እየተደረጉ ናቸው። በተመሳሳይ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የሚያስፈልጋቸውን ክህሎትና እውቀት ይዘው እንዲወጡ ሰፊ ሥራ መስራት እንዳለበት የሚያሳዩ ነገሮች መኖራቸውንም ነው አቶ አብደላ የሚገልጹት።

ሌላው በተግዳሮትነት መሪ ሥራ አስፈጻሚው የጠቀሱት የደህንነትና ሰላም ጉዳይ ነው። ለማንኛውም ኢንቨስትመንትና ልማት የሰላምና ደህንነት ጉዳይ ወሳኝ ነው ያሉት አቶ አብደላ፤ በልማቱ ላይ የተሰማሩ አካላት በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ ለማድረግ በመንግሥት በኩል ኃላፊነት ተወስዶ መስራት እንዳለበት አመላክተዋል። ለእዚህም በየደረጃው ያለው የመንግሥት አካል የሚገጥማቸውን ችግር በፍጥነት የመፍታት እና ችግር እንዳይገጥማቸው መከላከል ላይ መስራት እንደሚጠበቅበት አስታውቀዋል። ችግሮች ሲያጋጥሙ እንደሚችሉ ቀደሞ ተንብዮ ከመስራት አኳያ መሥራት ያለባቸው ተግባሮች እንዳሉም አስታውቀዋል።

አቶ አብደላ እንዳሉት፤ የሆርቲካልቸር ዘርፉ ገና ብዙ አልተሠራበትም። ብዙ መስራት ከተቻለ የምግብ ዋስትናን በሚገባ ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ አጠቃላይ በሀገር ደረጃ የሥራ ዕድል ከመፍጠር ጋር ተያይዞ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ለዚህ ደግሞ ስትራቴጂዎች ተቀርጸው ለመተግበር ጥረት እየተደረገ ነው።

የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት ረገድ ዘርፉ እንደሀገር ካለን እምቅ አቅም እስካሁን እያስገኘ ያለው ገቢ ብዙ እንዳልሆነም ጠቅሰው፣ በቡናና የሻይ ተክል ምርት ላይ በስፋት እየተሠራ እንዳለው ሁሉ በሆርቲካልቸር ሰብሎች ላይም በርካታ ሥራ መስራት እንደሚገባ አመልክተዋል።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው እንዳብራሩት፤ ሆርቲካልቸር ሲባል ብዙ ጊዜ አበባ ብቻ አድርጎ የመመልከት ሁኔታዎች አሉ። ሆርቲካልቸር ሲባል አበባ ብቻ አይደለም፤ የአትክልት፣ የሥራሥር ሰብሎች፣ የፍራፍሬ፣ የእጸ ጣዕም ፣ የቅመማቅመም፣ የቡና፣ ሻይና ሌሎችንም ሰብሎች የሚያካትት ነው።

‹‹እንደ አገር በሆርቲካልቸር ዘርፍ ለማልማት የሚያስችለው አቅም ከፍተኛ ስለሆነ ማንኛቸውንም በዓለም ላይ ሊመረቱ የሚችሉ የዘርፉን ሰብሎች አምርቶ ወደ ውጭ በመላክ መጠቀም ይቻላል›› ሲሉ አስታውቀው፣ ከዚህ አንጻር ብዙ አልተሰራም ይላሉ። ወደፊት በፖሊሲና ስትራቴጂዎች በመደገፍ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረጽ ሀገር በተሻለ መልኩ ተጠቃሚ መሆን የሚያስችላትን ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻልም አመልክተዋል።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው እንዳብራሩት፤ በግብርናው ዘርፍ ገቢን በማስገኘት ረገድ ከቡና ቀጥሎ የሆርቲካልቸር ሰብሎች በሁለተኛ ደረጃ እንደሚገኙ ይታወቃል። እንደ ሀገር ያለው አቅም ከዚህም በላይ ማምጣት እንደሚቻል ይጠቁማል። አሁን በአንድ ሺ. 892 ሄክታር መሬት ላይ እየለማ ካለው የአበባ ተክል ብቻ ነው 255 ሚሊዮን በላይ ዶላር የውጭ ምንዛሪ ማግኘት የተቻለው።

ይህን ልማቱ የሚካሄድበትን መሬት በእጥፍ ማሳደግ ቢቻል፣ ገቢውንም በእጥፍ ማሳደግ ይቻላል። የልማቱን ስፍራ ከዚህም በላይ እጥፍ ማድረግ ቢቻል ሦስት አራት እጥፍ ገቢ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል። በመሆኑም ከአበባ ብቻ ከአንደ ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ ይኖራል ሲሉ አቶ አብደላ አስገንዝበዋል።

ይህንን ለማሳካት ስትራቴጂክ ሆኖ መስራት እንደሚያስፈልግ አስታውቀው፣ ከክልሎች ጋር ተናብቦ የሚያስፈልገውን መሬት ለይቶ መስራትን እንደሚጠይቅ ገልጸዋል፤ ችግሮችን መፍታት ከተቻለ ዘርፉ በአጭር ጊዜ ዘርፉ ለውጥ ማምጣት የሚችል ፣ ለዜጎችም፣ ለሀገርም ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል።

ለውጭ ገበያ በርካታ የሆርቲካልቸር ምርት ለውጭ ገበያ ቀርቦ፣ ዝቅተኛ ገቢ እየተገኘ ያለበትን ሁኔታ በጥናት ላይ ተመስርቶ መቀየር፣ ዘርፉ ያለውን እምቅ አቅም በሚገባ ለይቶ መጠቀም መቻልና የአልሚዎችን፣ ሀገርንና ዜጎችን ተጠቃሚነት በሚገባ ማረጋገጥ ቀጣይ የዘርፉ የቤት ሥራዎች ናቸው።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የጥበበኛ ተብዬ ጥበበኞቹ ጥበብ እስከ ምን?

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አንዳንዴ ነገሮች ከመስመር ባለፉ ጊዜ በእጅጉ ያስተዛዝባሉ፡፡ እንዲህ አይነት አጋጣሚዎች ደግሞ የሰውን ልክና ማንነት ጭምር የሚጠቁሙ ናቸው። ሁሌም ቢሆን ለአንድ ጉዳይ ልኬታ ሲበጅለት፣ መስመር ሲዘረጋለት አመኔታው ይጎላል፡፡ አንዳንዶች ግን አጋጣሚውን ባገኙ ጊዜ ገደብ ይሉትን አያውቁም። ከንግግር ሳይቆጠቡ፣ የሚያወጡትን ቃል ሳይመርጡ እንዳሻቸው ይሆናሉ፡፡

ይህኔ ጀሮ አግኝተው ሊደመጡ የሚችሉት ለጥቂት አፍታዎች ብቻ ይሆናል፡፡ ከዚህ ያለፈው ጊዜ ግን ከመተዛዘብ አያልፍም፡፡ ሁሌም እነሱን ከሚሰሟቸው መሀል አብዛኞቹ ጉዳያቸውን ፍሬ ነገሬ አይሉትም። እንደውም አንዳንዶቹ የታዘቡትን በውስጣቸው ይዘው ስለ ድርጊት፣ ምግባራቸው ያፍሩላቸዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ስማቸውን እያነሱ መቀለጃ ፣ መዘባበቻ ያደርጓቸዋል፡፡

ሰሞኑን ከአንድ የማህበራዊ ገጽ ላይ አንድን ጉዳይ ስታዘብ ከረምኩ፡፡ እንደው ለቃሉ ያህል ‹‹ትዝብት›› ልበለው እንጂ ለሃሳቡ ከዚህም በላይ መገለጫ ቢኖረው እወድ ነበር፡፡ የትዝብቴ መነሻ በማህበራዊ ገጹ ላይ የተቀመጠው ዝርዝር ሃሳብ ነው፡፡ ይህ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ‹‹ይድረስ ›› የሚለው መልዕክት ለእኔ ከጥቅሙ ጉዳቱ፣ ከግንዛቤው ይልቅ በሀፍረት አፍ ማስያዙ አመዝኖብኛል፡፡

በየአፍታ ልዩነት በየቦታው ተሰንቅሮ የሚገኘውን መልዕክት አሁንም ማንበብ ይዣለሁ፡፡ ያለ አንዳች ከልካይ እርግጠኛ በሆነ ስያሜ ‹‹የጥበብ አገልግሎት›› የሚል ቃል የተቸረው ይህ መልዕክት መሰል ማስታወቂያ በምን አጋጣሚ በግል ቴሌግራሜ ገፄ ላይ እንደደረሰ አላውቅም፡፡ ለእኔም ቤተኛ ከሆነ ግን ከራርሟል፡፡ በየጊዜው አዳዲስ ሃሳቦችን ከምስል ጋር አቀናብሮ ብቅ እያለ ያስደንቀኛል፡፡

ከተጻፉት ዝርዝሮች መሀል ጥቂቱን እያነበብኩ በግርምታ ማስተዋሌን ቀጥያለሁ፡፡ በዚህ ገጽ ላይ ለመቁጠር የሚያዳግቱ ዝርዝር ሃሳቦች ተቀምጠዋል። አንዳንዶቹ የተለመዱና የሚታወቁ ናቸው፡፡ እኔን ያስገረሙኝ ግን ከተለመዱት ሁሉ ይለያሉ፡፡ አንደኛው እንዲህ ሲል ይጀምራል፡፡ ‹‹ለጥበብ ቤተሰቦች ከምንሰጣቸው አገልግሎቶች መሀል እነዚህ ይጠቀሳሉ››፡

ለግርማ ሞገስ፡-ይህ የጥበብ አይነት ግርማ ሞገስ የሌላቸውን በሙሉ ክብር የሚያላብስ፣ ከሌሎች በተለየ እይታን እንዲስቡ የሚያደርግ መስሎ የቀረበ የጥበብ አይነት መሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ለግርማ ሞገስ ተብሎ የተቀመጠው ሃሳብ አንድ ሰው በሚገኝበት ስፍራ ሁሉ ዓይነ ግቡ ሆኖ፣ ሚዛን ደፍቶ፣ ከሌሎች ሁሉ ልቆና በልጦ እንዲታይ የሚያደርግ ኃይል መሆኑ ነው። እንግዲህ በዚህኛው የጥበብ መንገድ አምኖ የሚጓዝ ቢኖር ‹‹ጥላ ቢስ ›› ይሉት ቃል በአጠገቡ ዝር አይልም ማለት ነው፡፡ በዚሁ እየተገረምኩ ወደ ሌላው ነጥብ ተሻገርኩ፡፡

**የታሰረ ሰው እንዲፈታ ለማድረግ**

ይህኛው ነጥብ እንደሚጠቁመው የታሰረ ሰውን በጥበብ የማስፈታት ኃይል የመኖሩን ሀቅ ነው፡፡ ማንም ሊናገረው እንደሚችለው የሚታሰር ሰው አስቀድሞ ወደ ቦታው ሲገባ በህግ አግባብ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ ጥበብ የሚባለው መላ ግን የተቀመጠውን ደንብና መመሪያ ሁሉ ጥሶና በጣጥሶ ታሳሪውን የማስፈታት ኃይል እንዳለው በግልጽ አስቀምጧል፡፡

ጉዳዩ በዚህ ብቻ አይቋጭም ፡፡ የጥበብ ጉዞው ቀጥሎ ራስን ወደ መከላከል ኃይል ይሻገራል፡፡ በዚሁ ማህበራዊ ገጽ በግልጽ እንደተቀመጠው ራስን በጥበብ የመከላከል ኃይል ለጥበበኞቹ ቀላል መሆኑ ሰፍሯል፡፡ ጉዳዩ በግልጽ እንደሚያሳየውም ሃሳቡ እንዲህ በሚል መገለጫ ሰፍሯል፡፡

**ጠላት እንዳይጎዳ የሚያደርግ**

ጠላት ምን ጊዜም ጠላት ነው፡፡ ራሱን ከመከላከል አልፎ ተቃራኒውን ለመጉዳት ወደ ኋላ የሚል አይደለም፡፡ አስቀድሞ እንደተጠቀሰው ግን የዚህ ጥበብ ኃይል የጠላት ተብየውን ጉልበት ውሃ አድርጎ የተቀናቃኙን ወገን ብርታት የሚረታ ነው፡፡ ይህም ጉልህ ርዕስ ተሰይሞለት በግልጽ ተቀምጧል፡፡

የጥበበኞቹ ራስን የማስተዋወቅ መንገድ በተለመደው አግባብ ቢሆን ኖሮ ይህ ጉዳይ ተነስቶ ሊያስተዛዝበን ባልቻለ ነበር፡፡ እስካሁን የተለመደውና አብዛኛው ሰው የሚረዳው በአንዳንዶች ፍላጎትና ስሜት ላይ የተመሰረተ አሰራር መኖሩን ነው፡፡ ለምሳሌ፡ - ለህመም፣ ለመስተፋቅር፣ ለዓይነጥላ፣ ለመፍትሄ ስራይ፣ ለዛር ውላጅ፣ ለኪንታሮት ህመምና ለመሳሳሉት እየተባሉ የሚዘረዘሩ ሃሳቦች ተለምደዋል፡፡ አሁንም ይህን አምኖ መቀበል ያለመቀበል የግለሰቦች ፍላጎትና ምርጫ ይሆናል ፡፡

ዘንድሮ ግን ጨዋታው ሁሉ ከነበረው ገፅታ በእጥፍ ተለውጦ በአስገራሚ መልኩ ለገበያ ይቀርብ ይዟል፡፡ አንድ በእጅጉ የደነቀኝን ጉዳይ ደግሞ ልምዘዝ፡፡ በውጭ ሀገራት ለሚኖሩ የሀገር ልጆች የተቀመጠውን የጥበብ ነገር፡፡

የጥበበኞቹ ኃይል ወንዝ ተሻግሮ፣ ባህር ሰንጥቆ ሌሎች ዓለማት ላይ ጭምር መከሰት ጀምሯል፡፡ በተለያዩ ገፆች ላይ በግልጽ እንደሰፈረው ይህ ጥበብ ውጭ ሀገራት ለሚኖሩ ወገኖች ሳይቀር መድረስ ችሏል፡፡

አሁንም የህግና የአሰራርን ጉዳይ መጥቀስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ “ህገወጥ የሚለውን ጉዳይ እንተወውና ‹‹ህጋዊ›› የሚለውን ነጥብ እናንሳ፡፡ ማንኛውም ሰው ከሀገር ሲወጣና በውጭ ሀገራት ሲኖር በተቀመጠው የህግ አሰራር ላይ ተመስርቶ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

የመኖሪያ ፈቃድም ይሁን የዜግነት መብት ይሏቸው አሰራሮች ሊከወኑ የሚችሉትም ህጉንና ህጉን ብቻ መሰረት አድርገው ነው፡፡ የጥበበኞቹ መላ ግን ይህን እውነታ ከስሩ የመመንገል ኃይል እንዳለው የሚጠቁም ሆኗል፡፡ በውጭ ሀገራት የሚገኙ የሀገር ልጆች የመኖሪያ ፈቃድ ባያገኙ፣ የሥራ ዕድልን ቢያጡ የጥበበኞቹ ጥበብ ተአምር ሰርቶ ሁሉንም በእጃቸው፤ በደጃቸው ያደርሳል።

ወዳጆቼ! በተለያዩ የማህበራት ገጾች ላይ በተደጋጋሚ እየተሰራጨ ያለው መረጃ በአስገራሚነቱ ወደር የለውም፡፡ አሁንም ይሆነኛል፣ ይጠቅመኛል የሚል ጠያቂ ቢኖር ፍላጎቱ የግሉ መሆኑ እንዳለ ይሁንና ሌሎችን ጉዳዮች ላንሳቸው፡፡

በነዚህ ገፆች ላይ እየተዋወቁ ካሉና ‹‹ጥበብ›› ናቸው ከተባሉ ጉዳዮች ውስጥ ብዙዎቹ እንዳስገረሙኝ ቀጥለዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ለህዝብ መስተፋቅር፣ ለመክሳት፣ ለገበያ፣ ለዕቁብ፣ ለሎተሪ፣ ለዱላ፣ ለስልጣን፣ ለቁማር፣ ለክርክር፣ ለድምጽ፣ ጠላትን ለማፍዘዝ በሚል የተቀመጡት የጥበብ አይነቶች፡፡

እነዚህ ጉዳዮች ታአማኒነታቸውና በድፍረት የመውጣታቸው እውነታ አስገራሚ የሚባል ነው። እንደውም አንዳንዴ ‹‹ዓይናችሁን ጨፍኑና እናሞኛችሁ›› የሚሉ ይመስላሉ፡፡

እንደ እኔ ሃሳብና አስተያየት ግን ማንም ሰው አንድ ጉዳይ በድምቀት ስለተባለና ስለተነገረለት ብቻ የመቀበል አመኔታ ሊኖረው አይገባም፡፡ እርግጥ ነው ሰዎች ሲጨንቃቸው፣ ሲቸገሩና መላ ሲያጡ ከእንዲህ አይነቶቹ አጋጣሚዎች ጋር ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን ውሃውን ከእሳቱ፣ ምርቱን ከግርዱ፣ ጥቅሙንም ከጉዳቱ መለየት ግድ ይላል፡፡

አሁን ላይ እየተያዘ ያለው ዘዴ የሰዎችን ደካማ ጎን በመሻት በፍላጎቶቻቸው ላይ አስልቶ መስራት ነው። ይህን ዘዴ አስቀድሞ መጠርጠር ያልቻለ ደግሞ ገንዘቡንና ጊዜውን በግልጽ ከማስረከብ ውጪ ምርጫ አይኖረውም፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ አይነት ተግባራት ሲከወኑ በግልጽ ካለመሆኑ ጋር በርካቶች ኪሳራቸውን የሚያዩት በስተመጨረሻ ይሆናል፡፡ እናም ወዳጆቼ! ‹‹ጠርጥር! ከገንፎም ውስጥ አለ ስንጥር›› የሚለውን አባባል ቀድሞ ማስታወሱ ይበጃል፡፡ አበቃሁ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ቀይ ባህርና የሁቲ አማጽያን ጥቃት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ባለፉት ሳምንታት በቀይ ባሕር በኩል በመርከቦች ጭነት ማጓጓዝ ፈታኝ ሆኗል። በኢራን የሚደገፉት የየመን ሁቲ አማጽያን በሰው አልባ አውሮፕላን እና በሚሳኤል መርከቦች ላይ ጥቃት እየፈጸሙ ነው።

ታጣቂዎቹ በተጨማሪም በጀልባ እና በሄሊኮፕተርም ጥቃት አድርሰዋል። አብዛኛውን የመን የሚቆጣጠሩት ሁቲዎች “በጋዛ እና በዌስት ባንክ ላሉ ፍልስጤማውያን ወንድሞች” ድጋፍ እንደሚሰጡ ገልጸዋል።

ወደ እስራኤል የሚጓዙ የንግድ መርከቦችን ዒላማ እንዳደረጉ ሲሆን፤ ቢቢሲ ባጣራው መረጃ መሠረት ሁቲዎች ጥቃት የሰነዘሩት በደቡባዊ ቀይ ባሕር ነው። ይህም በየመን ባሕር ዳርቻ በባብ ኤል-ማንዳብ መተላለፊያ ላይ ነው።

ወደ ኤደን ባሕረ ሰላጤ የሚጓዙ መርከቦች ላይም ጥቃት ተሰንዝሯል። ነገር ግን በጥቃቱ ዒላማቸውን የመቱት የተወሰኑት ብቻ ናቸው። ከእነዚህም መካከል እአአ ጥር 17 የተፈጸመው ጥቃት ይገኝበታል።

በዚህም በአሜሪካ መርከብ ላይ ነበር ጥቃቱ የተቃጣው። ነገር ግን መርከቡ በሁቲዎች ድሮን ጎኑ ላይ ቢመታም ጉዞውን ቀጥሏል።

ጥቃቱን የሚያሳይ ምሥል ያነሳው የሕንድ የባሕር ተዋጊ መርከብ ነበር። ይህም የሁቲዎችን ጥቃት ለመመከት ያለውን ትብብር ማሳያም ነው።

ሁቲዎች ትናንሽ ጀልባዎችን በመጠቀም መርከቦች ላይ ጥቃት ይሰነዝራሉ። ሄሊኮፕተር በመጠቀም መርከብ ላይ ጥቃት የሰነዘሩበትም ወቅት ነበር።

በሄሊኮፕተር መርከብ ላይ የወረዱት ጥቃት አድራሾች አንድ መርከብን አግተዋል። ጋላክሲ ሊደር



የተባለው መርከብ አሁንም በየመን ባሕር ዳርቻ እንደተያዘ ነው።

የየመን የእርስ በእርስ ጦርነት ከተጀመረ ወዲህ ከሀገሪቱ መንግሥት የተወሰዱ መሣሪያዎች በሁቲዎች እጅ ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት እንደሚለው፣ ከምሥራቅ እስያ በሲቪሎች አማካይነት የተገኙም መሣሪያዎች አሏቸው።

አብዛኞቹ ዘመናዊ ድሮኖች እና ሚሳኤሎች ግን ከኢራን እንደተገኙ በስፋት ይነገራል። አሜሪካ እንዳለችው፣ ከየመን ወደ ኢራን በዓሣ ማስገሪያ ጀልባ ተጭኖ እየተጓዘ የነበረ የሚሳኤል እና የአየር መቃወሚያ ይዛለች።

ወታደራዊ ተንታኞች እንዳሉት ኤምቪ ቤሻድ የተባለ የኢራን መርከብ ሁቲዎች ዒላማ እንዲመቱ እያገዘ ነው። ቀድሞ ማጓጓዣ የነበረው መርከብ አሁን የደኅንነት መቆጣጠሪያ መሆኑን ያስረዳሉ።

በቀጣናው የደኅንነት ቡድን የመሩት ክሪስ ፋረል እንደሚሉት፣ የተለያየ ቁሳቁስ የጫኑ መርከቦች ጥበቃ የሚደረግላቸው ቢሆንም ከአየር የሚደረግ ጥቃትን መከላከል የሚያስችል መሣሪያ ግን የላቸውም። ይህ በቀይ ባሕር በኩል የሚያቋርጡ “የንግድ መርከቦች ከረዥም ጊዜ በኋላ የገጠማቸው ከባድ ችግር ነው” ይላሉ።

ዓለም አቀፍ ምላሽ ከመጠናከሩ ጋር በተያያዘ አሜሪካ እና ዩናይትድ ኪንግደም በጋራ በየመን የሁቲ አማጽያን ይዞታዎች ላይ የአየር ጥቃት ፈጽመዋል።

በዚህም ሁለቱ ሀገራት የአማጽያኑን ወታደራዊ አቅም ለማዳከም ያለመ ጥቃት ነበር የሰነዘሩት። ሆኖም ግን የየመንን ሰፊ ተራራማ አካባቢዎች ሁቲዎች ይቆጣጠራሉ። መደበቅ የሚችሉትም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ወታደራዊ ተንታኞች ይናገራሉ።

ባለፈው ታኅሣሥ በአሜሪካ የሚመራ ወታደራዊ ጥምረት የንግድ መርከቦችን ለመጠበቅ እንደሚሠራ ተገልጿል። በዚህም ቀይ ባሕርን የመቆጣጠር ሥራ የሚሠሩ ሲሆን ዩናይትድ ኪንግደም ለዚህ ተግባር መርከብ እንደምታቀርብ አስታውቃለች።

ከአሜሪካ ጥምረት ውጪ እንደ ፈረንሳይ ያሉ ሀገራትም በቀጣናው መቆጣጠሪያ ጣቢያ አላቸው። የአሜሪካ የባሕር ኃይል ካፒቴን ብራድሊ ማርቲን እንደሚሉት የተለያዩ ዓለም አቀፍ አጋሮችን ማስተባበር ፈታኝ ነው።

ባሕሩ ላይ የሚከናወነውን ጥበቃ የሚያካሂዱትን መርከቦቹ ነዳጅ ሞልቶ መሣሪያ ማስታጠቅም ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃል። ከሁቲዎች የሚተኮሱትን እንደ ሲ ቫይፐር ያሉ ሚሳኤሎችን መከላከል በሚሊዮን ዶላር የሚያስወጣ ነው።

በተቃራኒው ሁቲዎች የድሮን ጥቃት ለመፈጸም የሚያወጡት በሺዎች የሚቆጠር ዶላር ነው። በርካታ ተቋማት መርከባቸው በቀይ ባሕር እንዳይጓዝ እያደረጉ ነው።

ይህ ማለት ደግሞ ኬፕ ኦፍ ጉድ ሆፕ በተባለው የአፍሪካ ዳርቻ መንገድ ለመጓዝ ከፍተኛ ወጪን ያወጣሉ ማለት ነው። ረጅሙን የውቅያኖስ ላይ ዙሪያ ጥምጥም መንገድ በማስቀረት በቀይ ባሕር ለመጓዝ የመረጡ ደኅንነታቸውን ለመጠበቅ አማራጮች እየተጠቀሙ ነው።

# የስማርት ዲፕሎማሲ ገጽታዎች፣ አተገባበርና ለኢትዮጵያ ያለው ጠቀሜታ

**መላኩ ሙሉዓለም ቀ.**
**በውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ተመራማሪ**
**melakumulu@yahoo.com**

ስማርት ዲፕሎማሲ ከዲጂታል ዲፕሎማሲ፣ ሳይበር ዲፕሎማሲና ቨርቹዋል ዲፕሎማሲ ጋር ብዙ የሚያመሳስሉት ጉዳዮች አሉት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ሁሉም የዲፕሎማሲ ዓይነቶች ቴክኖሎጂን በመጠቀም የዲፕሎማሲ ሥራ የሚከናወኑባቸው ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ስማርት ዲፕሎማሲ ከሌሎች የዲፕሎማሲ ዓይነቶች የላቀ ስፍራ ያለው ነው፡፡

በዋናነት ስማርት ዲፕሎማሲ መጠነ ሰፊ ዳታ (Big data–driven decision making) የሚፈልግና በትንተና ላይ የተመሠረተ የዲፕሎማሲ ሥራ ሲሆን የዲፕሎማቶች ውሳኔ የመስጠት አቅምና ፍጥነትን በማጎልበት የሚከናወን የዲፕሎማሲ ዘርፍ ነው። በመሆኑም ስማርት ዲፕሎማሲ ለማከናወን ጥልቅ መረጃዎችን አደራጅቶ ከሚይዝ አካል ጋር ተቀናጅቶ የሚሠራ እንጂ እንደሌሎቹ የዲፕሎማሲ ዘርፎች በጥቃቅንና በተበታተኑ መረጃዎች ላይ ተሞርክዞ የሚከናወን ዲፕሎማሲ አይደለም፡፡

ከነባሩ ዲፕሎማሲ (traditional diplomacy) የሚለይበትም በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም በዋናነት ብዙ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ነው፡፡ የነጋዴው፣ የሕዝቡ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት፣ የዲያስፖራ ማኅበረሰብ፣ የምሁራኑን፣ አሰላሳይ ተቋማትን እና የመሳሰሉትን በመረጃ እና ግብአቶች በማሳተፍ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሠራ ነው፡፡

ስማርት ዲፕሎማሲ ስፋትና ጥልቀት ያለው የዲፕሎማሲ ዓይነት ነው፡፡ ይህ ማለት እንደሳይበር ዲፕሎማሲ የሳይበር ደህንነት ላይ ብቻ ያጠነጠነ አይደለም፡፡ እንደ ቨርቹዋል ዲፕሎማሲ መለስተኛ መረጃዎችን በርቀት የመቀባበልና የውይይት ሥራ የሚሠራበት ብቻ አይደለም፡፡ በተመሳሳይም እንደ ዲጂታል ዲፕሎማሲ አነስተኛ መረጃዎች ላይ (not big data) የተንጠለጠለ አይደለም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ዘርፈ ብዙ የሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚሠራ ነው፡፡ ፐብሊክ ዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ፣ የአየርንብረት ዲፕሎማሲ፣ ሳይንስ ዲፕሎማሲ፣ ሰብዓዊ ዲፕሎማሲ(humanitarian diplomacy)፣ የጾታ ጉዳይ ዲፕሎማሲ(Gender Diplomacy)፣ የባህል ዲፕሎማሲ፣ የዲያስፖራ ዲፕሎማሲ፣ የጤና ዲፕሎማሲ እና የመሳሰሉት በስማርት ዲፕሎማሲ ተቀናጅተው የሚሠሩ ናቸው።

ይህ የዲፕሎማሲ አሠራር በሀገሮች ወይም በዓለም አቀፍ ተዋናዮች መካከል ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን ለማሳካት የተራቀቁ ቴክኖሎጂዎችን፣ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ትንተና እና የፈጠራ ቴክኒኮችን በመጠቀም የሚከናወን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ነው፡፡ በዲጂታል ዘመን ውስጥ የዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን እና የዲፕሎማሲ ሂደቶችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያግዝ ነው።

ዘመኑ የዋጀውን ዲጂታል መሣሪያዎችን፣ ማኅበራዊ ሚዲያዎችን እና የኢንፎርሜሽን እና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን (ICTs) በመጠቀም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋርም ውይይትን እና መድረኮችን ለማከናወን ያግዛል። እነዚህ መሣሪያዎች ዲፕሎማቶች ከብዙ ታዳሚዎች ጋር እንዲገናኙ፣ መረጃን በብቃት እንዲለዋወጡ እና ለዓለም አቀፍ ክስተቶች በቅጽበት ምላሽ እንዲሰጡ ያስችላቸዋል።

ውስብስብ የሆኑ ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን ለመፍታት ባህላዊ ዲፕሎማሲያዊ አቀራረቦች ሁልጊዜ በቂ ባለመሆናቸው ስማርት ዲፕሎማሲ ክፍተቶችን ይሞላል። በዘመናዊው ዓለም የዲፕሎማሲያዊ ተግባራት ውጤታማነትና ቅልጥፍና በማምጣት ዓላማን ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

ይህ ዘመናዊ ዲፕሎማሲ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስን በአግባቡ መጠቀምን ይጠይቃል። በመሆኑም ዲፕሎማቶች የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስንና ሌሎች ተዛማጅ ቴክኖሎጂዎች ላይ በቂ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ የስማርት ዲፕሎማሲ ሥራ ለማከናወን ያስችላቸዋል፡፡

ዲፕሎማቶች ስማርት ዲፕሎማሲን በመጠቀም የተለያዩ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ፡፡ የውጭ ፖሊሲ ውይይቶች ላይ ከዜጎች፣ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየት፣ መረጃን ለመሰብሰብ እና ለመተንተን፣ አዝማሚያዎችን ለመለየት እና በመረጃ የተደገፈ የፖሊሲ ውሳኔ ለመስጠት ይረዳል።

አዳዲስ አቀራረቦችን በማበረታታት እና ከተለያዩ መንግሥታት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተዋናዮች፣ የግሉሴክተር እና አካዳሚዎች ጋር በመመካከር ብሔራዊ ተግዳሮቶችን፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቶችን እና ፈጣን ምላሽ ዘዴዎችን በመጠቀም ቀውሶችን በብቃት ለመቆጣጠር እና ተጽዕኖአቸውን ለማቃለል ያግዛል።

የፐብሊክ ዲፕሎማሲ እና የባህል ልውውጥ በማድረግ፣ የዲጂታል ዘመቻዎች በመጠቀም የሀገርን መልካም ገጽታ ለማስተዋወቅ እና ዓለምአቀፍ ግንዛቤን ለማሳደግ፣ ዓለምአቀፍ የጋራ ተግዳሮቶችን በጋራ ለመፍታት በባለ ብዙ ወገን ድርጅቶች እና መድረኮችን ለመጠቀም፣ ከዲያስፖራ ማኅበረሰብ ጋር ተናቦ ለመሥራት ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡

ስማርት ዲፕሎማሲ ለሁለትዮሽና ለባለብዙ ወገን የዲፕሎማሲ ሥራ ያገለግላል። ስማርት ዲፕሎማሲ እንደሽብርተኝነት፣የሳይበርደህንነት፣ የሕዝብ ጤና እና ስደትን የመሳሰሉ ተሻጋሪ ችግሮችን ለመፍታትና በሀገሮች መካከል ትብብር ለመመስረት፣ ለዲፕሎማቶች ቀጣይነት ያለው የአቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል።

ዲፕሎማቶች በቴክኖሎጂ የተካኑ ከሆኑ በተለያዩ የዓለማችን ጫፍ ላይ የሚከናወኑ ተግባራትን በፍጥነት እንዲያገኙ፣ ከሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም ጋር ሊኖራቸው የሚችለውን መልካም ወይም ጎጂ ሁኔታዎችን ለመረዳትና ለመተንተን ያግዛቸዋል። የዲፕሎማቶችን ብቃት ለማሳደግ በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም ዙርያ ሥልጠና መስጠት ያስፈልጋል። ስማርት ዲፕሎማሲ ዲፕሎማቶች የተወሳሰቡ ዲፕሎማሲያዊ ተግዳሮቶችን በብቃት እንዲወጡ ያስችላቸዋል። እንዲሁም ማኅበራዊ ሚዲያን፣ ብሎጎችን፣ እና ሌሎች ዲጂታል መድረኮችን በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያግዛቸዋል።

መረጃዎችን በመሰብሰብ እና ትንታኔዎችን በማከናወን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችን የተሳኩ ያደርጋል። ተዛማጅ መረጃዎችን በመሰብሰብ እና በመተንተን፣ ዲፕሎማቶች ስለአዝማሚያዎች፣ የተለያዩ ሀገራት አቋሞች፣ አስተያየቶች እና ሊኖሩ ስለሚችሉ አደጋዎች ወይም ዕድሎች ግንዛቤዎችን ማግኘት ይችላሉ።

ዛሬ እርስ በርስ በተሳሰረ ዓለም ውስጥ ቀውሶች ሊፈጠሩ እና በፍጥነት ሊዛመቱ ይችላሉ። ስማርት ዲፕሎማሲ ለሚከሰቱ ቀውሶች ፈጣን እና ውጤታማ ምላሾች ለመስጠት ያግዛል። እነዚህን ክስተቶች በቅጽበት መከታተል፣ ዲጂታል መድረኮችን ለፈጣን ግንኙነት መጠቀምን እና ቀውሶችን በወቅቱ ለመፍታት ከዓለምአቀፍ አጋሮች ጋር መተባበርን ይጠይቃል።

የባህል ግንዛቤን በማስፋት ገር ኃይል (soft power) በሌሎች ሀገራት ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። የሀገርን ባህላዊ ቅርስ በቴክኖሎጂ በመታገዝ (ቨርቹዋል) ማሳየት፣ የባህል ልውውጥን ማስተዋወቅ እና የባህል ትብብርን መፍጠር ያስችላል። በአጠቃላይ ስማርት ዲፕሎማሲ ባህላዊ ዲፕሎማሲያዊ ልማዶችን ከዲጂታል ዘመን ጋር ለማጣጣም፣ ቴክኖሎጂን እና አዳዲስ አቀራረቦችን በመጠቀም ዲፕሎማሲያዊ ውጤታማነትን ለማጎልበት፣ ሰፊ ሕዝብን ለመድረስ እና ተግዳሮቶችን በቀልጣፋ እና ምላሽ ሰጪ በሆነ መንገድ ለመፍታት ያግዛል።

የተለያዩ ፌስቲቫሎች ለማዘጋጀትና ለበርካታ ሰዎች ተደራሽ በመሆን እና የባህል ልውውጥን በማድረግ የሀገርን ገፅታ ለማሳደግ ያግዛል። የባህል ቅርሶችን ለማስተዋወቅና ግንዛቤን በማሳደግ ቱሪስቶችን ለመሳብ፣ የሀገራችንን የባህል ቅርሶች ለማሳየት፣ የገር ኃይሏን መጠቀምና ማሳደግ እና ከሌሎች ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር ያስችላታል።

የዲያስፖራ ማኅበረሰቦች እውቀትና ተሞክሮ በአግባቡ ለመጠቀም ያስችላል። ለዚህም ሥራ ከዲያስፖራዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የማሰባሰብ፣ የመተንተን፣ ለሀገራቸው ሊያበረክቱ የሚችሉትን ጉዳዮች ለመለየት፣ ከማኅበረሰቡ ጋር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ለመወያየት፣ አቅምንና ችሎታን ለማስተባበር ያግዛል፡፡ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትን በማሳደግ፣ ንግድና ኢንቨስትመንትን በመሳብ እና ዲያስፖራዎች የባህል አምባሳደሮች ሆነው እንዲያገለግሉ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ስማርት ዲፕሎማሲ በሳይበር ተፅእኖ እና ተግዳሮቶች አሉበት። ዲፕሎማቶች በዲጂታል መድረኮች ሲጠቀሙ የመረጃ ደህንነት ማረጋገጥ ወሳኝ ነው። በዲጂታል ዘመን የሳይበር ደህንነት እና የኢንተርኔት አስተዳደር ወሳኝ ዲፕሎማሲያዊ ጉዳዮች ሆነዋል። ስማርት ዲፕሎማሲ የሳይበር ጥቃት እንዳይደርስበት ጥንቃቄን ይሻል፡፡ የመረጃ ጥበቃና የሳይበር ወንጀል መከላከል ከስማርት ዲፕሎማሲ ጋር ጎን ለጎን አብረው መሄድ አለባቸው፡፡

ስማርት ዲፕሎማሲ ምስጢራዊነት ያለው መረጃን ለመጠበቅ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ ዲጂታል የመገናኛ መስመሮችን እና የሳይበር ደህንነት ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ለመፍታት ጠንካራ ፖሊሲዎችን፣ የሕግና ደንብ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ይጠይቃል። በዲፕሎማቶች ላይ ያለ እምነትን ሊያሳጡ እና ዲፕሎማሲያዊ ጥረቶችን ሊያበላሹ የሚችሉ የተሳሳቱ መረጃዎችን እና የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዎችን መከላከል አስፈላጊ ነው። ስማርት ዲፕሎማሲ ሲከናወን የሀሰት መረጃን እና የሳይበርን ተፅእኖን የመከላከል እና የመቀነስ ስልቶችን መጠቀም ይጠይቃል።

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ስማርት ዲፕሎማሲ ለሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት አጋዥ ይሆናል፡፡ እነዚህም

- የኢኮኖሚ ዕድሎችን ለመለየት፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር ያለውን ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ለማሳደግ ያግዛል። በተለይም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ኢትዮጵያን የኢንቨስትመንት መዳረሻ ለማድረግ ያግዛል። የኢንቨስትመንት መድረኮችን እና ኮንፈረንሶችን ማደራጀት እና የተሳለጠ ሂደቶችን ለማከናወን ያስችላል፣
- የኢትዮጵያን የንግድ ግንኙነት ለማስፋፋትና ለወጪ ንግዱ ምቹ የገበያ ተደራሽነት እንዲኖር ያስችላል። ኢትዮጵያ ምርቶቿንና አገልግሎቶቿን ወደ ውጭ ሀገራት ማስተዋወቅ እና ወደ ዓለምአቀፍ ገበያዎች በስፋት ለመግባት ያግዛታል፣
- ስማርት ዲፕሎማሲ ውጤታማ የቀውስ አስተዳደር (Crisis Management) ለማከናወን ያግዛል። እንደተፈጥሮ አደጋዎች፣ ግጭቶች ወይም ወረርሽኞች በተከሰቱ ጊዜ፣ ዲፕሎማቶች ሕዝቡን ለማሳወቅ፣ መመሪያ ለመስጠት እና የዓለምአቀፍ ምላሽ ጥረቶችን ለማስተባበር በፍጥነት እና በትክክል ለመገናኘት ያግዛል፡፡ ለተጎዱ ሕዝቦች እርዳታ ከዓለምአቀፍ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች ተዋናዮች ጋር ሰብአዊ ምላሾችን ለማስተባበር እና የተጋላጭ ሕዝቦችን ችግር በመቅረፍ ሰብአዊ ቀውሶችን ለመፍታት ያግዛል፣
- ከአየር ንብረት ጋር የተያያዙ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ትብብርን በማመቻቸት፣ እውቀትን በመለዋወጥ እና ሀብትን በማሰባሰብ የዲፕሎማሲውን ሚና የአየር ንብረት ዲፕሎማሲን ለማከናወን ያግዛል፣
- በፀረ-ሽብርተኝነት ትብብር፣ መረጃ መጋራት እና በክልል የጸጥታ ተግባራት ለማከናወን ያስችላል። ኢትዮጵያ ከዓለምአቀፍ አጋሮች ጋር በመተባበር የጸጥታ መዋቅሯን ማጠናከር፣ የድንበር ደህንነትን ማጎልበት እና ለቀጣናው መረጋጋት አስተዋፅዖ ማድረግ ያስችላታል፣
- በአፍሪካ ቀንድ ኢኮኖሚያዊ ውህደት፣ መሠረተልማት ዝርጋታ እና የጋራ የጸጥታ ጥረቶች ባሉ ውጥኖች ክልላዊ ትብብርን ለማጠናከር ያስችላል። ከዓለምአቀፍ አጋሮች ጋር በመተባበር የገንዘብ ድጋፍን፣ቴክኒካል እውቀትን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ማግኘት ያስችላል፣
- የዲፕሎማቲክ መንገዶችን በመጠቀም ኢትዮጵያ አዳዲስ የካፒታል ምንጮችን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማመቻቸት ለኢኮኖሚ እድገትና ልማት አስተዋፅዖ ማድረግ ያስችላታል፣
- ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የዲያስፖራ ማኅበረሰብ በውጭ ሀገር አሏት። ስማርት ዲፕሎማሲ የዲያስፖራ ተሳትፎን እምቅ አቅም በመጠቀም፣ የእውቀት ሽግግርን እና የባህል ልውውጥን ለማስተዋወቅ ያስችላል፣
- ኢትዮጵያ የበለጸገ የባህል ቅርስ እና ልዩ የቱሪስት መስህቦች አሏት። ስማርት ዲፕሎማሲ በባህልና ቱሪዝም ዲፕሎማሲ ላይ ትኩረት በማድረግ የኢትዮጵያን ዓለምአቀፋዊ ገጽታ ለማሳደግ እና ዓለምአቀፍ ጎብኚዎችን ለመሳብ ያስችላል። እንዲሁም የባህል ዲፕሎማሲ ውጥኖችን፣ የኢትዮጵያን የባህል ብዝሃነት፣ጥበብና ወግ በማሳየት፣ የቅርስ ቦታዎች እና የቱሪዝም መስህቦችን በምናብ (ቨርቹዋል) ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ማስተዋወቅና ጎብኚዎችን ከተለያዩ ዓለማት ለመሳብ ያስችላል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ስማርት ዲፕሎማሲ በመጠቀም ብሔራዊ ጥቅሟን ለማሳደግ፣ ለማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ልማት አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ አጋርነቶችን ለመፍጠር ያስችላታል።

ለማጠቃለል ያህል ስማርት ዲፕሎማሲ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በዲፕሎማሲ ውስጥ ያለውን ሚና አጉልቶ ይጠቀማል። እንዲሁም በዲጂታል ዘመን የሚቀርቡትን ዕድሎችን፣ የጋራ እውቀትን እና ሀብቶችን በመጠቀም ሀገራዊ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ችግሮችን ለመፍታት እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ያግዛል። ስማርት ዲፕሎማሲ በፍጥነት በመለዋወጥ ላይ ባለው ዓለምአቀፍ ሁኔታ ውስጥ ብሔራዊ ጥቅሞችን ለማስከበር ያግዛል።

ከተለምዷዊ ዲፕሎማሲያዊ መስመሮች ባለፈ ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጋር መቀራረብን ይጠይቃል። ይህም ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፣ ከአካዳሚክ፣ ከአሰላሳይ ተቋማት (think tank) እና ከግል ድርጅቶችና ወዘተ ጋር መተባበርን ይጨምራል። ብዙ ተዋናዮችን በማሳተፍ ስማርት ዲፕሎማሲ ዘርፈ ብዙ ፈተናዎችን በትብብር መንገድ ለመፍታት ያስችላል።

ለዚህ ሁሉ መሠረት የሚሆነው ከዲፕሎማሲ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መጠነ ሰፊ ዳታ(Big Data) ማደራጀት፣ የዳታ ትንታኔ የማከናወን፣ አስፈላጊ የቴክኖሎጂ ግብአቶችን የማሟላት፣ የዲፕሎማቶችን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም አቅም የማጎልበት ተግባራትን ማከናወን የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

# ባለውለታዎቻችን

# በአዲስ አበባ ጉልህ አሻራቸውን ያሳረፉት የላንድስኬፕ አርክቴክት

ክብረአብ በላቸው

በመሬት አቀማመጥ (በላንድስኬፕ) አርክቴክት የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የሆኑት ኢንጂነር ጌታቸው ማህተመስላሴ፤ ከ95 አመት በፊት በ1921ዓ.ም ነበር የተወለዱት፡፡ አባታቸው ብላቴን ጌታ ማህተመስላሴ ወልደመስቀል በፈረንሳይ ሀገር ሶርቦርን ዩኒቨርሲቲ የአፈርና የእርሻ ምርምር ሙያ ትምህርትን በመከታተል በአግሮ ኢኮኖሚ የተመረቁ ሊቅ ነበሩ፡፡ ለሀገርና ለትውልድ ጠቃሚ የሆኑ ከ18 በላይ መጽሐፍትን ለንባብ ያበቁ ሰው ናቸው፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው በልጅነታቸው ያደጉት የእናታቸው ታላቅ እህት ከሆኑት ከወይዘሮ ሮማን ወርቅ ጋር ነበር። የቄስ ትምህርታቸውንም የጀመሩት እዚሁ አክስታቸው ቤት ነው፡፡ የአክስታቸው ባል ደጃዝማች አባ ሻውል በጣሊያን ወረራ ጊዜ ሲሞቱ ትምህርታቸውን ለመቀጠል እንዲያመቻቸው ወደ ወላጆቻቸው ቤት ተመለሱ፡፡

በጊዜው ክቡር ብላቴን ጌታ ማህተመስላሴ የልዑል አልጋ ወራሽ እንደ ራሴ ሆነው ይሠሩ ነበር፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን የተከታተሉት ደሴ በሚገኘው በወይዘሮ ስህን ትምህርት ቤት ነበር፤፡፡ ኢንጂነሩ በገቡባቸው ትምህርት ቤቶች ሁሉ የላቀ ውጤት በማስመዝገብ በተደጋጋሚ ክፍሎችን እየዘለሉ አልፈዋል፡፡

ወደ አቃቂ ሚሲዮን ገብተው በመማር ላይ እያሉም የ2ኛ ደረጃ መግቢያ ፈተና ሲመጣ፤ ያለደረጃቸው ፈተናውን ከወሰዱት በእድሜ ትንሹ እርሳቸው ነበሩ። ፈተናውን ያልፋሉ ተብሎም አልተጠበቀም ነበር፡፡ ኢንጂነር ጌታቸውም ፈተናውን «አልፋለሁ» የሚል ግምት ቢኖራቸውም፤ « እኔን ከእነዚህ ትልልቅ ተማሪዎች ጋር ማን አብሮ ይመለከተኛል?» ብለው አስበው ስለነበር፤ ፈተናውን ማለፋቸው ሲነገራቸው ማመን ተስኗቸው ነበር።

ኢንጂነር ጌታቸው የአምቦ እርሻ ኮሌጅን የተቀላቀሉት በ17 አመታቸው ነበር፡፡ የአምቦ እርሻ ኮሌጅ ተማሪዎችን የሚቀበለው በጊዜው ከባድ የሚባለውን ፈተና ተፈትኖ እንጂ እንዲሁ «ተማሪ አጣሁ» በሚል ማንንም አይቀበልም ነበር። ስለዚህ ኢንጂነር ጌታቸው የመግቢያ ፈተና መውሰድ ነበረባቸው። ፈተናውን የወሰዱት ብዙ ተማሪዎች ቢሆኑም ያለፉት ግን በጣም ጥቂቶች ነበሩ። ኢንጂነር ጌታቸውም ፈተናውን ካለፉ ጥቂቶች ውስጥ አንዱ ሆኑ። ትምህርታቸውንም በ1938 ጀምረው ከ 7 አመት በኋላም በ1944 ለመመረቅ ችለዋል፡፡


ኢንጂነሩ በአምቦ እርሻ ኮሌጅ በነበራቸው ቆይታ ከአስተማሪዎቻቸው የተረዱትን ትምህርት እርሳቸው በገባቸው መሰረት በራሳቸው የቋንቋ አጠቃቀም ለፈተናዎች መልስ መስጠታቸውን አስተማሪዎቻቸው ያደንቁላቸውና ያበረታቷቸው ነበር።

ኢንጂነር ጌታቸው በፈተና ውጤታቸው ከክፍላቸው ውስጥ ብዙውን ጊዜ ከአምስት እስከ ሰባተኛ ደረጃ ይወጡ ነበር። በመጨረሻም ከእርሻ ኮሌጅ በአጠቃላይ የእርሻ ሙያ በተመረቁበት ጊዜ ከ45 ተማሪዎች የ5ኛ ደረጃ ይዘው አጠናቀቁ። ኢንጂነሩ በነበራቸው ተሰጥኦ በአምቦ የእርሻ ትምህርት ቤት እያሉ ትምህርት ቤቱን ለማደስ ጨረታ ሲወጣ፤ አብሮ በመጫረት ለተደጋጋሚ ጊዜ አሸንፈው ሌሎች ተማሪዎችን ከዛው በመቅጠር ትምህርት ቤቱን ያድሱ ነበር። በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ጄኔሬተሮችን በኃላፊነት ይጠግኑ ነበር።

በዚሁ ኮሌጅ ባገኙት የቅየሳ ሙያ የአውራ ጎዳና ባለስልጣን ተብሎ በአሜሪካ መንግሥት በተቋቋመው መስሪያ ቤት ውስጥ በረዳት መሐዲስነት ደረጃ በቀያሽነት ተቀጠሩ፡፡ በለቀምት፣ ቀጥሎም በይርጋለም የድልድይ መሐንዲስ ሆነው ከአለቃቸው ከአሜሪካዊው መሀንዲስ ጋር ሲሰሩ ቆዩ፡፡

በመቀጠልም ከኮምቦልቻ አሰብ በሚሰራው መንገድ ላይ የዲስትሪክት ኢንጂነር ሆነው ካገለገሉ በኋላ ወደ እርሻ ሚኒስቴር በግዴታ ተዛወሩ፡፡ ፖይንት ለውሃ ሀብት ልማት የተሰኘ ድርጅት በአሜሪካ መንግሥት ሲቋቋም እርሻ ሚኒስቴርን ወክለው አብረው እንዲሰሩ ስለተመደቡ፤ ከአሜሪካዊው አለቃቸው ጋር በኢትዮጵያ ባሉት በበጋ በማይደርቁ መለስተኛ ወንዞች ላይ በተደረገው ጥናት ላይ አንዱ ተካፋይ ሆኑ፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ፖይንት ለውሃ ሀብት ውስጥ ይሰሩ በነበሩበት ወቅት፤ በኢትዮጵያ ባሉ በተለያዩ ክፍለ ሀገሮች ወንዞች ወዳሉበት የመሄድ ዕድል አግኝተዋል። የቆቃ ግድብና የብሉ ናይል እንዲሁም የሌሎችን ወንዞች የውሃ መጠን፣ የውሃውን ፍጥነት፣ የውሃውን ይዘት የሚሄደውን




የአፈር መጠን እንዲሁም ለምን አገልግሎት መዋል እንደሚችል በመመርመር ሥራውን ከሚያጠናው አካል ጋር አብረው ሠርተዋል።

ወደ ዋናው መስሪያ ቤት ተጠርተውም የመስሪያ ቤቱ የተሸከርካሪ ክፍል ምክትል በመሆን እያገለገሉ ሳሉ፤ በ1949 ዓ.ም የነጻ የትምህርት እድል አግኝተው ወደ ምዕራብ ጀርመን ተልከው ከይዘን ሀይም ራይን በሚገኘው የትምህርትና የምርምር ኢንስቲትዩት ተመድበው በላንድስኬፕ አርኪቴክቸር በከተማ ፕላኒንግ በዲግሩ ሰለጠኑ፡፡

በትምህርታቸው ያሳዩትን ጥሩ ውጤትና ትጋት በመመልከት ትምህርት ቤቱ ለአምቦ እርሻ ኮሌጅና ለእርሻ ሚኒስቴር በጻፈው ደብዳቤ ወደ ጀርመን ሀኖቨር ዩኒቨርሲቲ ተልከው ዶክትሬታቸውን እንዲቀጥሉ ሃሳብ ቀረበ። ኢንጂነር ጌታቸው ግን «በተማርኩት ትምህርት ሀገሬን ባገለግል ይሻላል፡፡» ብለው ወደ እናት ሀገራቸው ተመለሱ። የበለጠ ሊሰሩ የሚችሉት ማዘጋጃ ቤት ስለነበር ወደ ማዘጋጃ ቤት ተዛውረው ሥራ ጀመሩ፡፡

ኢንጂነር በአዲሱ ሙያቸው በመጀመሪያ እንዲሰሩ የተመደቡት በማዘጋጃ ቤቱ ውስጥ ፓርክና መናፈሻ በሚባል ክፍል ውስጥ ነበር፡፡ ይህንን ክፍልና ሌሎቹን ጨምሮ ይመሩ የነበሩት ኢጣሊያዊው ኢንጂነር ኮሎምቦ ነበሩ፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው ይህን ስራቸውን በጀመሩበት ወቅት የአፍሪካ መሪዎች ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ ተብሎ ከተማይቱ ከፍተኛ ውጥረት ላይ የነበረችበት ጊዜ ነበር፡፡

የህንጻ ግንባታው መንገዱ ጽዳቱ ሁሉም ትኩረት የተሰጠው ነበር፡፡ ነገር ግን በጊዜው የአፍሪካ አዳራሽ ህንጻ አካባቢ ያለው ስፍራ የተጎሳቆለ እና ጽዳት የጎደለው ነበር፡፡ ይህን ቦታ ጽዱ እና ያማረ ለማድረግ ቀደም ብሎ በኢንጂነር ኮሎምቦ እና በኢንጂነር ጌታቸው የተዘጋጀ ፕሮጀክት ነበር። በጊዜውም ኢንጂነር ጌታቸው ወደ ማዘጋጃ ቤት እንዲገቡ የተደረገው ይህን እቅድ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ነበር፡፡ ዕቅዱ ዋናው መሀንዲስ ኮሎምቦና ረዳቱ ጅኦሜትራ ደሩኝ ከሥር ከሥር ጥናቱን እያጠኑ፣ የጥናቱን ዝርዝር ለኢንጂነር ጌታቸው በማስተላለፍ ሥራውን እንዲሠራ ነበር።

ይህ አካሄድ ያልጣማቸው ኢንጂነሩ በመጀመሪያ ስለ አጠቃላይ ፕሮጀክቱ ለመረዳት የተዘጋጀው ፕሮጀክት እንዲሰጣቸው ጠየቁ፤ ይህ ፕሮጀክት ደግሞ ለወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉስ ቀርቦ ሊጸድቅ ጥቂት ቀናት ብቻ ቀርቶት ነበር፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው ግን ፕሮጀክቱን ሲመለከቱት ከብዙ አቅጣጫ ብቁ ሆኖ አላገኙትም ነበር።

ስለዚህ በጊዜው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ለነበሩት ዘውዴ ገብረሥላሴ፤ «ይህ ፕሮጀክት ልክ አይደለም አንደኛ የግንብ ብዛት አለው፤ ሁለተኛ ከፍተኛ ወጪ ይጠይቃል፣ ሶስተኛ ለመኪና ማቆሚያ የተከለለው ቦታ የተዘጋጀው 250 መኪና ብቻ ማስተናገድ እንዲችል ተደርጎ ነው፡፡ ይህንን ቦታ ከዛ በተሻለ ዘመናዊ በሆነ መልኩ በመገንባት ለብዙ መኪናዎች ማቆሚያ ጭምር ማድረግ ይቻላል፡፡ ስለዚህ `እኔ ላጥናው፡፡» በማለት ይጠይቃሉ።

ከንቲባው የጊዜው መቃረብ ያሳስባቸው ስለነበር «ጊዜ የለንም፤ ይህ ጥናት ብዙ ጊዜ ፈጅቷል በፕሮጀክቱ መሠረት ቶሎ ተብሎ ወደ ተግባር መግባት ይኖርብናል» ቢሉም ኢንጂነር ጌታቸው ግን በሃሳባቸው በመጽናት «እኔ ሌትና ቀንም ቢሆን ሠርቼ በቶሎ አደርሳለሁ፡፡» በማለት ትንሽ ቀን እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ፤ ከንቲባውም ኢንጂነሩ ለፕሮጀክቱ የሰጡትን ከፍተኛ ትኩረት በማስተዋል ጥያቄያቸውን ተቀብለዋቸዋል።

ኢንጂነር ጌታቸው በገቡት ቃል መሠረት ቀንና ሌት በመስራት በጥቂት ቀናት ውስጥ ንድፉን ሠርተው ለከንቲባው አቀረቡ። ከንቲባው የቀረበላቸውን ንድፍ ሲመለከቱ በንድፉ በእጅጉ ተሳቡ፤ ሲመለከቱም ለ250 መኪና ማቆሚያ ታስቦ የነበረው ቦታ ወደ 525 መኪና ለማስቆም መቻሉን ተገነዘቡ። በበፊቱ ፕሮጀክት ላይ የነበሩ አላስፈላጊ ግንቦች ቀርተው፤ ሁሉ ነገር መልክ መያዙን በመረዳት ክቡር ከንቲባው በኢንጂነር ጌታቸው በቀረበው ንድፍ ተደስተው በቶሎ እንዲያልቅ ባዘዙት መሠረት ኢንጂነሩ ፕሮጀክታቸውን በፍጥነት በመጨረስ ለከንቲባው አቀረቡ። ይሄው ፕሮጀክት በኢንጂነር ጌታቸው አስረጅነትና በከንቲባው አማካኝነት ለንጉሱ ቀርቦ ሥራ ላይ ዋለ። ኢንጂነር ጌታቸውም ፕሮጀክቱ ለመሥራት ጨረታ ካሸነፈው የጣሊያን ኩባንያ ጋር የሥራው ተቆጣጣሪ መሀንዲስ በመሆን፤ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አደራሽ እውን ማድረግ ቻሉ።

ኢንጂነር ጌታቸው በመቀጠል የተረከቡት የጽዳትና ፕላን ክፍል ኃላፊነትን ነበር፡፡ ይህንን የሥራ ኃላፊነት እንደተረከቡ ካከናወኑት ሥራውን ለማቀላጠፍና ውጤታማ ለማድረግ የተወሰኑ ማሻሻያዎች አድርገዋል። ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- ሥራዎች በሥራ ጣቢያቸው መልክ አስይዘዋል፡፡ ለየሥራውም በተለያዩ ቦታዎች ብቃት አላቸው ብለው የሚያምኑባቸውን ሙያተኞችና ሠራተኞች መደቡ፣ ተከማችቶ ለነበረው ሥራ የሠራተኛ ኃይል መደቡ፣ ከውዝፍ ሥራ የዕለት ተዕለት ሥራ ቅድሚያ እንዲሰጠው አደረጉ።

ኢንጂነር ጌታቸው በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ክለሳ የተለያዩ ሥራዎችን ሰርተዋል፡፡ ዘጠኝ መቶ ሺህ ነዋሪዎችን ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀውን ፕላን የህዝብ ቁጥሩ ዕድገቱን ባማከለ መልኩ እንዲዘጋጅ አድርገዋል። ዋናውን የከተማ እምብርት ወደ ብሔራዊ ትያትርና ወደ ፖስት ቤት እንዲወርድ አድርገዋል። በዚህን ወቅት ቤት ሰሪዎች ቤታቸውን ሲሠሩ በፕላኑ መሠረት እንዲሰሩ ውል እንዲገቡ አድርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በከተማዋ መሀል የሚገኙ ወንዞች የሚያስከትሉት መጥፎ ጠረን ለማስቀረት ወደ ፊት የሚገነቡ ህንፃዎች ወንዞችን እየሸፈኑ ማለፍ እንዳለባቸው ኢንጂነር ጌታቸው ባጠኑት የአሥር ዓመት ማስተር ፕላን ላይ ተቀምጧል።

ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ ወደ ውጭ ልከው ካስተማሯቸው አርክቴክቸሮች አንዱ የሆኑት ኢንጂነር ጌታቸው፤ የአንበሳ አውቶቡስ ሞዴል ያመጡ ፣ የአዲስ አበባ የወንዞች ዳርቻዎችና የአዲስ አበባ ከተማ ቤቶች ፕላን ሠርተው ያቀረቡ ባለሙያ ናቸው። በህይወት ዘመናቸው የካ ተራራ ጫፍ የሚገኘውና እየፈራረሰ ያለው ዋሻ ሚካኤልን ከመፍረስ ለመታደግ ብዙ ጥረት አደርገዋል።

ከ10 አመት በላይ በማዘጋጃ ቤት ካገለገሉ በኋላ ወደ መንግሥት ንብረት ድርጅት የተዘዋወሩት ኢንጂነር ጌታቸው፤ ቀጥለውም የብሔራዊ ሀብት ልማት ኮርፖሬሽን ኃላፊ በመሆን እየሰሩ የማስፋፋት ስራቸውን ተያያዙት፡፡ ነገር ግን እንደፈለጉት አልቀጠሉም። ምክንያቱም አብዮቱ ፈነዳ፤ ደርግ ለስምንት አመት አሰራቸው፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው ደርግ ለስምንት አመት ቢያስራቸውም ታላቅ ወንድማቸውን ያለ ምንም ፍርድ ቢገድልባቸውም ተሰደው ወደ ውጭ መሄዱን አልፈለጉትም፡፡ ይልቁንም በልዩ ልዩ የግል ወይም ዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ በሀገራቸው ለማገልገል ወሰኑ፡፡

ኢንጂነር ጌታቸው ወይዘሮ የሺሀረግ ዋዝጎን አግብተው ሁለት ልጆችን ያፈሩ ሲሆን፤ የህይወት ታሪካቸው መጽሐፍ ከ12 አመት በፊት በ156 ገጽ ታትሞ የወጣ ሲሆን ፤ የራሳቸውን ሰነድ በመያዝም ለብዙዎች አርአያ ሆነዋል፡፡ ኢንጂነር ጌታቸው ህዳር 30 2016 በተወለዱ በ95 አመታቸው ህይወታቸው ያለፈ ሲሆን፤ የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸውም በቅድስት ስላሴ መንበረ ጸባኦት ቤተክርስቲያን ታኅሣሥ 1 ቀን 2016 ተፈፅሟል። እኛም እኚህን የሀገር ባለውለታ ነፍስ ይመር እንላለን።

# ስፖርት



## በአስደናቂ ክስተቶች የታጀበው የአፍሪካ ዋንጫ



ብርሃን ፈይሳ

ለዋንጫ ተጠባቂዋ የአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጅ ኮትዲቯር ከውድድሩ በጊዜ የተሰናበተችበት፣ ታላላቅ ቡድኖች አጣብቂኝ ውስጥ የገቡበት፣ ያልታሰቡ ቡድኖች ተጠናክረው የተገኙበት፣ ጥሎ ማለፉን የሚቀላቀሉ ቡድኖችን አስቀድሞ መገመት አዳጋች የሆነበት 34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ በድራማዊ ክስተቶች ተሞልቶ መካሄዱን ቀጥሏል፡፡ ገናና ስም ያላቸው አፍሪካዊ ቡድኖች እንደታሰቡት አለመሆናቸውን ተከትሎም ዋንጫ ሊያነሳ የሚችል አዲስ ቡድንን ያስተዋውቅ ይሆን የሚለውም የበርካቶች ጥያቄ ሆኗል፡፡

በቀድሞ የእግር ኳስ ጀግናቸው ዲዲየር ድሮግባ እና ሕዝባቸው ፊት ከውድድሩ መሰናበታቸውን ያረጋገጡት ዝሆኖቹ፤ ባልተጠበቀ ሁኔታ በኢኳቶሪያል ጊኒ በተቆጠሩባቸው 4 ግቦች እፍረትን ተከናንበዋል፡፡ የአጀማመራቸውን እንጂ የአጨራረሳቸውን አለማማር ተከትሎም ደጋፊዎች ከስታዲየም ውጪ ያገኙትን አውቶቡስ በመሰባበር ጭምር ቁጣቸውን ገልጸዋል፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ ከምድብ ጨዋታዎች አልፈው ተፎካካሪነታቸውን ማስመስከር ያልቻሉት ጋናዎች ስንብታቸውን ተከትሎ፤ ደጋፊዎቻቸው የቡድኑ አባላት ከስታዲየም ሲወጡ ጠብቀው ንዴታቸውን አንጸባርቀዋል። ለዋንጫ ተጠባቂው ሌላኛው ቡድን ካሜሮን ውጤትም በተመሳሳይ ውድድሩን ልዩ መልክ እንዲኖረው ካደረጉ ክስተቶች አንዱ ነው፡፡

ከሞዛምቢክ፣ ጋና እና ኬፕቨርዴ ጋር አቻ በመለያየት በሰበሰበቻቸው ሦስት ነጥቦች ወደ ቀጣዩ ዙር መሸጋገሯን በመጨረሻ ሰዓት ያረጋገጠችው ግብጽም በውድድሩ ከአስገራሚ ቡድኖች አንዷ ናት፡፡ የበርካታ ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫ ባለድሏ ግብጽ በሁለቱ ጨዋታዎች ተጨማሪ ሰዓት ያስቆጠረቻቸው ግቦች ታድገዋታል፡፡ እንደ መርፌ ቀዳዳ በጠበበው የማለፊያ ዕድል የተጠቀሙት ፈርኦኖቹ ከጋና ጋር 2 እኩል በተለያዩበት ጨዋታ ጉዳት የደረሰበት ብሔራዊ ጀግናቸው ሞሃመድ ሳላህ፤ አገግሞ ወደ አፍሪካ ዋንጫው የመመለስ ዕድል እንደሌለው መሰማቱ ራስ ምታት ሆኖባቸዋል፡፡

ወሳኞቹና የመጨረሻዎቹ የምድብ ጨዋታዎች ዛሬም ቀጥለው የሚከናወኑ ሲሆን፤ ምድብ አምስትን በመምራት ላይ የምትገኘው ማሊ ናሚቢያን ትገጥማለች፡፡ ለማለፍ አቻ መውጣት ብቻ የሚጠበቅባት ደቡብ አፍሪካ ደግሞ በአንድ ነጥብ በደረጃ ሰንጠረዡ መጨረሻ ላይ ተቀምጣ ወደ ቀጣይ ምዕራፍ መተላለፏ ጥያቄ ውስጥ ከገባው ቱኒዚያ ጋር ትጫወታለች፡፡ በምድብ ስድስት መሪዋ ሞሮኮ ከዛምቢያና ዴሞክራቲክ ኮንጎ ጋር በእኩል ነጥብ ከተለያየችው ዛምቢያ ጋር ትገናኛለች፡፡ በመጀመሪያው ጨዋታ በሞሮኮ የ3 ለምንም ሽንፈት የደረሰባትና የመመለሻ ቲኬቷን አስቀድማ የቆረጠችው ታንዛኒያ ደግሞ ጠንካራ ተፎካካሪ ከሆነችው ዴሞክራቲክ ኮንጎ ጋር የስንብት ጨዋታዋን ታከናውናለች፡፡

ኮትዲቯርን ጨምሮ ከየምድባቸው ሦስተኛ ደረጃን በመያዛቸው 16ቱን መቀላቀል ከተሳናቸው ቡድኖች አራቱ ምርጥ ሦስተኛ በመሆን ሁለተኛውን ዙር የመቀላቀል ዕድላቸውን የሚጠብቁም ይሆናል፡፡

## የስፖርት ታሪክ አዋቂው ስንብት

ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ፣ ጸሐፊ እና የቀድሞው የእግር ኳስ ተጫዋች ገነነ መኩሪያ ‹‹ሊብሮ›› የቀብር ሥነሥርዓት ዛሬ በ9፡00 በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይፈጸማል፡፡

መጋቢት 5 ቀን 1957 ዓ.ም በይርጋለም ከተማ የተወለደው ገነነ አብዛኛውን የልጅነት ጊዜውን ያሳለፈው በሻሸመኔ ከተማ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን በተከታተለበት አጼ ናዖድ ትምህርት ቤት ለስፖርትና ጋዜጠኝነት መሠረት የጣለ ሲሆን፤ የእግር ኳስ ችሎታውን በማዳበርም የተለያዩ ቡድኖችን ተቀላቅሏል፡፡

ከተግባረ ዕድ በጄነራል መካኒክነት ከተመረቀ በኋላም ለሜታ ቢራ እግር ኳስ ቡድን እየተጫወተ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ይጽፍ ነበር። በእግር ኳስ ተጫዋችነት ዘመኑም እስካሁንም የሚታወቅበትን ‹‹ሊብሮ›› የሚል ቅጽል ስም አትርፏል፡፡

ከእግር ኳስ ተጫዋችነት ከተሰናበተ በኋላ ያሉትን ሦስት አስርት ዓመታት ደግሞ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን በስፖርት ጋዜጠኝነት ሠርቷል፡፡ የሊብሮ ጋዜጣ ባለቤት የሆነው ገነነ በተለይ በቴሌቪዥን በሚያቀርባቸውና ታሪክን በሚያወሱ ዝግጅቶች ከፍተኛ ተወዳጅነትን አትርፏል፡፡

የኢትዮጵያን ስፖርት ጠንቅቆ በማወቅና በታሪክ አዋቂነቱ በበርካቶች ዘንድ ‹‹ተንቀሳቃሽ ቤተመጻሕፍት›› ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፤ ኢህአፓ እና ስፖርት (ከ1 እስከ 3)፣ ፍትሃዊ የጠጅ ክፍፍል፣ ሊብሮ ኢትዮጵያዊ ስልጠና፣ መኩሪያ፣ … የተባሉ መጻሕፍትን ለአንባቢያን አበርክቷል፡፡ ለእግር ኳሱ ላበረከተው የላቀ አስተዋጽኦም በአዲስ አበባ በተካሄደው የካፍ ኮንግረስ ላይ የረጅም ዘመን አገልግሎት ሜዳይ ተበርክቶለታል።

ባለ ትርዳር እና የሁለት ልጆች አባት የሆነው፣ ተወዳጁ እግር ኳስ ተጫዋች፣ ጋዜጠኛ እና ጸሐፊ ገነነ መኩሪያ ‹‹ሊብሮ›› ባደረበት ሕመም በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ ጥር 14/2016 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል። የቀብር ሥነሥርዓቱም ዛሬ በ9፡00 በመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ይፈጸማል።



ተወዳጁ የስፖርት ጋዜጠኛ፣ ጸሐፊ እና የቀድሞው የእግር ኳስ ተጫዋች ገነነ መኩሪያ፤


### የጣውላ ምርት ግልጽ ጨረታ ሽያጭ ማስታወቂያ
### የጨረታ ቁጥር OFWE/XA02/2016

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት በእያንዳንዱ የጣውላ ዓይነት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል፡፡

**ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ**

1. በአርሲ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
2. በባሌ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
3. በቦረና ጉጂ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያዎች ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
4. በፊንፊኔ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
5. በሐረርጌ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
6. በኢሉአባቦራ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
7. በጂማ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት የእንጨት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤
8. በወለጋ ደንና ዱር እንስሳት ቅ/ጽ/ቤት የእንጨት በተለያዩ የእንጨት መሰንጠቂያ ላይ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ጣውላ፤

1. የጣውላ የቤትና የቢሮ እቃዎችና ተዛማጅ የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸው ድርጅቶች እና ግለሰቦች እንዲሁም Tin number ያላቸውና እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ ስለ ጨረታው ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ የጨረታ ሰነድ ለእያንዳንዳቸው 200/ ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ቀበና ሼል /አይል ሊቢያ/አጠገብ በሚገኘው የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ዋና መ/ቤት 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 201 እና ጨረታው በሚወጣበት በጂማ ቅ/ጽ/ቤት (ጂማ) በኢሉአባቦራ ቅ/ጽ/ቤት (መቱ) በአርሲ ቅ/ጽ/ቤት (አርሲ ነጌለ) ፊንፊኔ ቅ/ጽ/ቤት (ፊንፊኔ) በሐረርጌ ቅ/ጽ/ቤት (ጭሮ) በቦረና ጉጂ ቅ/ጽ/ቤት (አዶላ) በባሌ ቅ/ጽ/ቤት (ጎባ) በወለጋ ቅ/ጽ/ቤት (ግምቢ) በመግዛት በጨረታው መሣተፍ ይችላሉ፡፡
2. ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣ ሲሆን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት ክፍት ሆኖ ይቆያል፡፡
3. ጨረታው የሚዘጋበትና የሚከፈትበት ትክክለኛው ቀንና ሰዓት በጨረታው ሰነድ ውስጥ ይገለፃል፡፡ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (Bid bond) የሚሆን ያቀረቡትን ጠቅላላ ዋጋ 5% በማስላት በድርጅቱ ዋና መ/ቤት የምትጫረቱ አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ባንኮች፤ በቅ/ጽ/ቤት የምትጫረቱ መ/ቤቱ ከሚገኝበት ከተማ በባንክ በተረጋገጠ ደረሰኝ (cpo) ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0111240249 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር 0111240249 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡**

**የኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት**



### ለሚመለከተው ሁሉ

የጨረታ ቁጥር DCE/EM/176/2023 ማራዘሚና መክፈቻ ቀን ስለማሳወቅ

ኢንተርፕራይዛችን ለአላጌ ግብርና ማሰልጠኛ ተቋም ፕሮጀክት አገልግሎት የሚውል “Compound light fitting and Pole” ግዥ አስመልክቶ በግልፅ ጨረታ ቁጥር DCE/EM/176/2023 ግብዣ መደረጉና ጨረታው ጥር 10 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚከፈት የተገለጸ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ ጨረታውን ማራዘም አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ጨረታውን የገዛችሁ ተጫራቾች የማራዘሚያ ደብዳቤ ከኢንተርፕራይዙ ግዥ ቡድን ቢሮ መውሰድ የሚትችሉ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ጨረታው ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ይዘጋል

ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡15 ይከፈታል

ተጫራቾች የመጫረቻ ሠነዶቻቸውን ከጨረታ መዝጊያና መክፈቻ ቀንና ሰዓት በፊት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

**አድራሻ፡- የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ**

**የቀጥታ ስልክ ቁጥር 0114-40-34-34**

**ማዞሪያ 0114-42-22-70/71/72**

**E-mail አድራሻ Info@dce-et.com**

**ድረ ገፅ አድራሻ www.dce-et.com**

**ፖ.ሳ.ቁ 3414 ፋክስ ቁ. 0114-40-04-71/0114-42-07-46**

**ወሎ ሰፈር የቀድሞው ኖጌሳ ግቢ**

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ሚኒስቴር የመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ**